**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2021-11-17

# þÿ --3Ê •ce `p (! è è í ( f

þÿ -e(u, ¤L+s

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/12913

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

**ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋካሊቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ፣ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም**

# *ማርክሳዊ ንባብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች*

**በ**

**ኤፍራታ ክብረት**

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

ባህር ዳር

*ማርክሳዊ ንባብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች*

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋካሊቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና *ሥነ-ጽሑፍ* አማርኛ ትምህርት ክፍል ፣ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

### ለአማርኛ *ሥነ-ጽሑፍ* ኤም.ኤ.ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ኤፍራታ ክብረት

አማካሪ፡ ተስፋማርያም ገ/መስቀል (ዶ/ር)

ጥቅምት ፣ 2014 ዓ.ም

## ሂዩማኒቲስ ፋካሊቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ፣ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

*ማርክሳዊ ንባብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች*

በ

ኤፍራታ ክብረት

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| --------------------- | --------------------- |
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| --------------------- | --------------------- |
| የፈታኝ ስም | ፊርማ |
| -------------------- | -------------------- |
| የፈታኝ ስም | ፊርማ |

# ማረጋገጫ

ይህ “ማርክሳዊ ንባብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች” በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን፣ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ________________

ፊርማ _______________________

የቀረበበት ጊዜ________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን የማስተርስ  ትምህርት እንድማር እድል የሰጡኝን መቅደላአምባ ዩኒቨርሲቲን እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ። በመቀጠል መረጃዎችን በመስጠት ፣ የኔን ስህተት በተደጋጋሚ በማረም ይህን ጥናት የተስተካከለ መልክ እንድኖረው የረዳኝን አማካሪዬን ዶ/ር ተስፋማርያም ገብረመስቀልን ከልብ አመሰግናለሁ።በተጨማሪ ይህን ስራ በምሰራበት ጊዜ “አይዞሽ” እያላችሁ ከጎኔ ለነበራችሁ ፣ ምክራችሁን ለለገሳችሁኝ ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

ምስጋና ..... i

አጠቃሎ ..... iv

ምዕራፍ አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ..... 5

1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ..... 5

1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ..... 5

1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ..... 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 6

1.6 የጥናቱ ወሰን ..... 6

1.7 የአጠናን ዘዴ ..... 7

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት ..... 8

ምዕራፍ ሁለት ..... 9

ክለሳ ድርሳናት ..... 9

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ..... 9

2.1.1 የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ምንነት እና ታሪካዊ ዳራ ..... 9

2.1.2 ማርክሲዝምና ሥነ ጽሁፍ (Marxism and Literature) ..... 10

2.1.3 ሥነ ጽሁፍና ላዕላይ መዋቅር (Literature and Superstructure ) ..... 12

2.1.4 ሥነ ጽሁፍና ርዕዮተ ዓለም (Literature and Ideology) ..... 13

2.1.5 ቁስ አካላዊነት (Materialism) ..... 15

2.1.6 መደብ (class) ..... 16

2.1.7 ስርአተ ጾታ (gender ) 23
2.2 የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ 24
ምዕራፍ ሶስት 27
ትንተና 27
3.1 የልቦለዶቹ አጽመ ታሪክ 27
3.2 ርዕዮተ ዓለም በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ 29
3.2.1 ሃይማኖት በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች 30
3.2.2 ስርአተ ፆታ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች 33
3.2.3 ቁስ አካላዊነት በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች 38
3.2.4 መደብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች 42
ምዕራፍ አራት 48
ማጠቃለያ 48
ዋቢ ጽሑፎች 50

# አጠቃሎ

*ይህ “ማርክሳዊ ንባብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች” በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ በአንድ የዘመን ክስተት ውስጥ ስለተነጸባረቁ ሥነ-ጽሁፋዊ ርዕዮተ ዓለሞች ፣ መደብ እና ቁሳዊነት የማርክስን ፍልስፍና እንደ ማያ በመጠቀም በአለማየሁ ገላጋይ የሥነ-ጽሁፍ ስራዎች ላይ የተደረገ ሂሳዊ ትንተና ነው። ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማካሄድ ምክንያት የሆነው በማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ዙሪያ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናታዊ ጽሁፎች አብዛኛኛዎቹ በደርግ ዘመን በተጻፉ ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ የተደረጉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በውጭ ቋንቋ በተጻፉ ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ የተደረጉ በመሆናቸው ከዘመን አንጻር የኢሃዴግን ዘመን ፤ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎችን ሂሳዊ ትንተና በማድረግ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል ነው።የዚህ ጥናት ዓላማ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳባዊ የሥነጽሁፍ እሳቤ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች ላይ እንዴት እንደተንጸባረቀ ማሳየት ነው። ለትንተና የተመረጡት ረጅም ልቦለዶች “አጥቢያ”(1999)፣ “በፍቅር ስም”(2009) እና “ታለ በእውነት ስም”(2011) ናቸው። እነዚህን ልቦለዶች ለመምረጥ ጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲሆን  ይህን ዘዴ ጥቅም ላይ እንድውል  ያደረጉት ምክንያቶች አንደኛው በማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ዙሪያ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች አብዛኛዎቹ በደርግ ዘመን በተጻፉ ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ የተደረጉ በመሆናቸው እነዚህ ሥነ ጽሁፎች የተጻፉበት ዘመን የኢህአዴግ ዘመን በመሆኑ ከዘመን አንጻር ያላቸውን ተንጸባራቂነት ለማየት ታልሞ ሲሆን ሁለተኛው ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎቹ የሚያነሷቸው ይዘቶች ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ በመሆናቸው ጥናቱ ከተነሳበት አላማ አንጻር ተገቢውን ውጤት የሚያስገኙ መሆናቸው ነው። በልቦለዶች ላይ የማርክሲዝምን ንድፈ ሃሳብ መታገዢያ በማድረግ የቴክስት ትንተና ተደርጓል።በትንተናውም ልቦለዶች  በተጻፉበት ዘመን አንጸባርቀው ያለፉትን ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ቁስ አካላዊና መደባዊ  ክስተቶች ከየልቦለዶቹ የተመረጡ የገጸ-ባህሪያት ምልልሶችን ነቅሶ በማውጣት ማሳየት ተችሏል። በዚህ ሂደት ሃይማኖታዊ የሆኑ እሳቤዎች ከሃይማኖትነታቸው በዘለለ ዝቅትቅኛ ማህበረሰብ በከፍተኛው የማህበረሰብ ክፍል አማካኝነት ለብዝበዛ እና ለስራ ፈትነት የመዳረግ ሁኔታ ሲያንጸባርቅ ተስተውሏል። ስርአተ ጾታንም በተመለከተ ማህበረሰብ ባወጣው የጾታ ህግ መሰረት(ወንድነት ወይም ሴትነት) ሴቶችን “መስራት አይችሉም” በሚል ምክንያት በኢኮኖሚ ስርአቱ ሴቶች የበታች እንደሚሆኑ እና ጭቆና እንደሚደርስባቸው ለመመልከት ተችሏል። በመሆኑም በማርክሲስቶች እሳቤ “ሥነ ጽሁፎች የርዕዮተ አለም ማንጸባረቂያ ይሆናሉ” የሚሉት ባንድም ይሁን በሌላ መልኩ በሥነ ጽሁፋዊ ስራዎቹ ውስጥ መታየት ችለዋል። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት እያንዳንዳቸው ልቦለዶች  በህብረተሰቡ ውስጥ የሚከወኑ ሃይማኖታዊ ፣ ስርአተ ጾታዊ ፣ ቁስ አካላዊ እና መደባዊ የሆኑ ርዕዮተ ዓለማዊ እሳቤዎችን ማሳየት እንደቻሉ አመላክቷል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሥነጽሑፍ በማንኛውም የሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን የሚያሳይ ነው። ማሳየትም ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በእያንዳንዱ የህይወቱ ምዕራፍ ውስጥ ስለሚከሰቱበት ገጠመኞች ይተነብያል ፣ አቅጣጫ ይሰጣል። ሥነጽሑፍ ከሰው ልጅ የኑሮ ዘይቤ ጋር የተሳሰረ ነው። የሥነጽሑፍንና የማኅበረሰብን ትስስር በተመለከተ (ዘሪሁን ፤ 2009 ፣ 7) የሚከተለውን ብሏል። "ሥነጽሑፍ የአንድን ማኅበረሰብ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መልኮችን ከማሳየቱም በላይ ቅርጹ በሚፈቅደው መሰረት ግለሰቦችና ህዝቦች ከእነዚህ ከሶስቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት አሰራርና ሁኔታ ያንጸባርቃል።" ሥነጽሑፍ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር እጅጉን የተቆራኘ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ጥናቶች በሥነጽሑፍ ላይ ይካሄዳሉ። ምክንያቱም ሥነጽሑፍን ማጥናት የሰውን ልጅ ሕይወት ውጣ ውረዶች ፣ ገጠመኞች ፣ ሥነልቡናዊና አዕምሯዊ ጣጣዎች ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብሮች ፣ ወግና ባህሎች ማጥናት ስለሆነ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሥነጽሑፍ ጥናትና ትችትም እጅጉን ተስፋፍቶ ይገኛል።

"ሥነጽሑፋዊ ትችት አንድን የሥነጽሑፍ ስራ የማጥናት ወይም አንብቦ የመረዳትና የመተርጎም ተግባር ነው" (Tyson, 2006 : 6)። ትችት ሲባል በሥነጽሑፋዊ ስራው ውስጥ የተደበቀውን ሚስጥር ፣ ያለውን አንድምታ ፣ የሚያሳየውን ጥቁምታና መሰል ነገሮች አውጥቶ ማሳየት እንጅ የስራውን ደካማ ጎን ማጉላት አይደለም። ይህንንም ሃሳብ ዘሪሁን (2009 ፣ 353) ራኒ ዌሌክን ጠቅሶ እንዳስቀመጠው ሥነጽሑፋዊ ትችት የተወሰኑ ደራሲያንን ሥነጽሑፋዊ ስራዎች ተመልክቶ ጥናካሬ እና ድክመታቸውን በመለየት የሚመዝንና የሚዳኝ ሳይሆን ሥነጽሁፉን በአንዱ ወይም በሌላው ሥነጽሁፋዊ ትወራ መነጽር እየተመራ የልቦለዱን ባህሪ ፣ አፈጣጠር ፣ ተግባርና ከሌሎች ሰዋዊ ጉዳዮች ጋር ስላለው ግንኙነት ፣ ስለ ውበቱና ቅንጅቱ በተጨባጭ የሚያሳይና ተንትኖ ማስረዳት የሚችል መሆኑን ነው። ሥነጽሑፋዊ ሀያሲ ድርሰቱ ከበቀለበት ባህልና ዘመን ውጭ ሊሰጥ የሚችለውን ትርጉም መለየት፣ መገንዘብና

በተጨባጭ ማስረዳት መቻል አለበት፡፡ ሃያሲያን ይህንን ሲያደርጉ ግን በዘፈቀደ አይደለም፡፡ የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን በመጠቀም ነው፡፡

ንድፈ ሃሳቦቹ ከተለያዩ የእውቀት ዘርፎች ሊፈልቁ ይችላሉ፡፡ ከፈለቁበት የእውቀት ዘርፍ በመነሳት ሥነጽሑፍን ለማየት የሚያስችሉ መነጽሮች በመሆን ያገለግላሉ፡፡ እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች በሥነጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ የሚገለጹ ጉዳዮችን ለመረዳት ያስችላሉ፡፡ ንድፈ ሃሳቦች ከተግባቦት ባለፈ በስራው ውስጥ በሥነጽሁፍ ጥበብ የተገለጹ ድብቅ ሚስጥሮችን የመግለጽ እና የማሳየት ተግባር አላቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ አነሳሱ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የማኅበረሰብ ስርዓቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን በዚህ ዘመን በማኅበረሰብና በሥነጽሑፍ ጥናት ውስጥ የሚዘወተር ነው፡፡

> ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ በካርል ማርክስ(1818-1883)የተመሰረተ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ በኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሌላ አባባል የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ኢኮኖሚያዊ በሆኑ የመደብ ክፍፍሎች እና ርእዮተ አለም ላይ ያተኮረ ነው የሚል ነው፡፡በማርክስ እምነት ደመወዝ ተከፋይ ወይም ዝቅተኛ መደብ ባለበት የመደብ ትግል ይኖራል በትግሉም ሰራተኛው መደብ አሸናፊ ይሆናል የሚል ነው (Tyson, 2006:53)፡፡

የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ከሚያጠነጥንባቸው ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የማኅበረሰብ ሁነቶች ጋር ተያይዞ ርዕዮተ ዓለም ፣ መደብ ፣ የመደብ ትግል ፣ ቁሳዊነት ፣ ብዝበዛ ፣ ኢኮኖሚያዊ ኃይል ፣ ባይተዋርነት ፣ አብዮት … የመሳሰሉ የማኅበረሰብ ጉዳዮች እየተነሱ ይንጸባረቁበት ነበር፡፡ ይህም አንድ የፍልስፍና ዘርፍ በመሆኑ እንደሌሎች ፍልስፍናዎች ሥነጽሑፍን ለመተቸት የሚያስችል የእውቀት ዘርፍ በመሆን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከዚህ ንድፈ ሃሳብ መከሰት ጋር ተያይዞ ማርክሳዊ ሂስ በመባል ከዚህ በላይ የተነሱትን ማጠንጠኛ ነጥቦች በሥነጽሑፍ ውስጥ ደራሲያን እንዴት ማንጸባረቅ እንደሚችሉ ፤ እነዚህን መሰል ጉዳዮችን ለምን ዓላማ በሥነጽሑፍ ውስጥ እንደሚያነሷቸው ፤ የዚህ ንድፈ ሃሳብ መከሰት በደራሲያን እና በሥነጽሑፍ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳደረ ፤ ሥነጽሑፋዊ ስራው በተጻፉበት ዘመን ምን ዓይነት ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ስርዓቶች እንደነበሩ ፤ ሥነጽሁፋዊ ስራው በተጻፈበት ዘመን በተደራሲያን ላይ ሥላሳደረው ተጽዕኖ … የመሳሰሉ ጉዳዮችን በማንሳት በማንኛውም ሥነጽሑፋዊ ስራ ላይ ትንታኔ ይሰጥበታል፡፡ ታይሰን (2006) ስለ ማርክሳዊ ሂስ እና ከሥነጽሁፍ ጋር ስላለው መስተጋብር የሚከተለውን ትላለች፡፡

> ማርክሳዊ ሂስ የማርክስን ፍልስፍና መሰረት ያደረገ ሲሆን ድርሰት የርዕዮተ ዓለም መግለጫና የልዕለ መዋቅር (ሱፐር ስትራክቸር) አካል አድርጎ ያያል። ድርሰትን ከመደብ አንጻር ስለሚያይ ሃያሲው ድርሰቱ ምን ያህል የህዝቡን ህይወት በተጨባጭ ገልጿል ፣ የህዝቡን ችግር አመላክቷል ፣ ለውጧል ፣ አንቅቷል ፣ የመደብ ጠላቱን ተዋግቶበታል የሚሉ ጉዳዮችን ያነሳል። ድርሰቱንና ገጸ በህሪያቱን ከመደብ አንጻር በገዥና ተገዥ ከፋፍሎ ያጠናል(Tyson 2006 : 68)።

በመሆኑም ይህ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ እንዴት እንደተንጸባረቀ ማሳየት የዚህ ጥናት ዋነኛ ስራ ነው። ለዚህ ስራ የተመረጡት ረጅም ልቦለዶች *አጥቢያ(*1999 *ዓ.ም*) ፣ *በፍቅር ስም(*2009 *ዓ.ም*) እና *ታለ በእውነት ስም*(2011 *ዓ.ም*) ናቸው። አለማየሁ በርካታ ልቦለዶችን የጻፈና በርካታ አንባቢያንንም ያፈራ አንጋፋ ደራሲ ነው ማለት ይቻላል። ከደረሳቸው ስራዎቹ ውስጥ "ኩርቢት" ፣ "አጥቢያ" ፣ "ቅበላ" ፣ "በፍቅር ስም" ፣ "ታለ በእውነት ስም" ፣ "መለያየት ሞት ነው" ፣ "የስብኃት ገ/እግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት" ፣ "ኢህአዴግን እከሳለሁ"፣ "የፍልስፍና አፅናፎት"፣ "መልክአ ስብሐት" ፣ "የብርሃን ፈለጎች" እና "ወሪሳ" የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው። ከእነዚህ ሁሉ ስራዎች ግን ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሆነው የተገኙት ሶስቱ ብቻ በመሆናቸው ትኩረቴ ከእነሱ ላይ ብቻ ይሆናል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከላይ በዳራው ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ የመደብ ልዩነቶች ላይ እንደሚያተኩርና ከዚህ ንድፈ ሃሳብ ጋር ተያይዞ የተከሰተው ማርክሳዊ ሂስም ድርሰት የላዕላይ መዋቅር ( Supersturucture) መገለጫ እና አካል ነው የሚል አንድምታ እንዳለው አይተናል። ይህም በEagleton (2003 : 5) ላይ እንዲህ ተቀምጧል። "ኪነ ጥበብ ለማርክሲዝም የኅብረተሰቡ ላዕላይ መዋቅር አካል እና የርዕዮተ ዓለም ማንጸባረቂያ ነው።" ይላል። Tyson (2006: 68) በበኩሏ "ማርክሳዊ ሂስ ድርሰትን ከመደብ አንጻር ስለሚያይ ድርሰቱ ምን ያህል የህዝቡን ህይወት በተጨባጭ ገልጿል፤ የህዝቡን ችግር አመላክቷል፤ ለውጧል፤ አንቅቷል፤ የመደብ ጠላቱን ተዋግቶበታል የሚሉ ጉዳዮችን ያነሳል" ትላለች። በመሆኑም እነዚህን መሰል የኅብረተሰብን ሁነቶች የሚያንጸባርቁ ሥነጽሑፋዊ ጭብጦችን የሚያነሱ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች የሉም ወይ? የሚለው ጥያቄ ተፈጥሮብኝ ነበር። ይህን በምፈትሽበት እና ልቦለዶችን በማነብበት ጊዜ ከዚህ ጋር በተያያዘ አሁን ጥናት የማካሂድባቸውን ልቦለዶች ከላይ የጠቀስኳቸውን እና መሰል ጉዳዮች ይዘው አገኘሁ። ልቦለዶቹ የአለማየሁ ገላጋይ የስነጽሁፍ

ስራዎች ናቸው፡፡አለማየሁ በበርካታ ስራዎቹ ቀላል የሚባሉ በሥነጽሁፍ ስራዎች ውስጥ እምብዛም ትኩረት ያልተሰጠባቸው ነገር ግን የማኅበረሰቡ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ በኢኮኖሚ የበላይና የበታችነት ፣ መገለልና አድሎ ፣ ኢኮኖሚያዊ ኃይል (economic power) ፣ ባይተዋርነት ፣ ርዕዮተ ዓለም ...ወዘተ የመሳሰሉ ጭብጦች በሰፊው ተንጸባርቀውባቸዋል፡፡ ስለዚህ ለምን እነዚህን ልቦለዶች ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ አንጻር አላያቸውም? በሚል ይህን ጥናት ላጠና የተነሳሁበት አንዱ ምክንያት ነው፡፡

የአለማየሁ ስራዎችን ካነበብኩ በኋላ በማርክሲዝም ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ፡፡ ከንድፈ ሃሳቡ ጋር በተያያዘ በጥናት መልክ የተዳሰሱት የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች በቂ የሚባሉ አይደሉም፡፡ ጥናቶች ቢኖሩም እንኳን አብዘኛኛዎቹ በውጭ ቋንቋ በተጻፉ ልቦለዶች ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡ በርግጥ አድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚካኤል ፍቅረማሪያም እና በምስራቅ ታረቀኝ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በትንደድ እድሜ በአማርኛ ቋንቋ በተደረሱ ረጅም ልቦለዶች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች አሉ፡፡ እነዚህም የሚካኤል (A STUDY OF THE INFLUENCE OF MARXISM ON BEALU GIRMA'S THREE NOVELS: HADDIS, YEKEY KOKEB TIRI, AND DERASIW ፣ 2008) በሚል ርዕስ በሶስት የበአሉ ግርማ ልቦለዶች ላይ የተሰራ ሲሆን የምስራቅ (ALIENATION IN THREE AMHARIC NOVELS: Fɨk'ɨr ɨskä Mäk'abɨr, Adäfrɨs and Kadmas Bašagär ፣ 2002) በሚል ርዕስ በሃዲስ አለማየሁ ፣ በዳኛቸው ወርቁና በበአሉ ግርማ ልቦለዶች ላይ የተሰራ ነው፡፡ በእነዚህ ጥናቶች ሚካኤል ርዕዮተ ዓለም(ideology) ላይ ትኩረት በማድረግ ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ አንጻር በሶስት የበአሉ ግርማ ልቦለዶች ላይ ትንታኔ ሰጥቶበታል፡፡ በጥናቱም የማርክስ ንድፈ ሃሳብ እንዴት በበአሉ ድርሰቶች ላይ ርዕዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ማሳየት ችሏል፡፡ ምስራቅም ባይተዋርነት(alination) ላይ ትኩረት በማድረግ በሃዲስ አለማየሁ ፣ በዳኛቸው ወርቁ እና በበአሉ ግርማ ድርሰቶች ውስጥ ያሉ ገጸ ባህሪያት የሚደርስባቸውን መገለል ወይም ባይተዋርነት(alination) የማርክስን ንድፈ ሃሳብ መሰረት በማድረግ ማሳየት ችላለች፡፡ የትንደድ ጥናትም (ሙስና በአፈላማ እና ያልታበሱ እንባዎች ፣2012) በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናትም አፈላማ እና ያልታበሱ እንባዎች በሚሉ ሁለት የአሰፋ በቀለ ስራዎች ላይ ሙስና እንዴት እንደተገለጸ የማርክስን ንድፈ ሃሳብ መሰረት በማድረግ አሳይታለች፡፡

እነዚህ ጥናቶችን ስመለከት ከጭብጥ አንጻር ርዕዮተ ዓለምን ፣ ባይተዋርነትን እና ሙስናን ብቻ የሚያነሱ ናቸው፡፡ ከጊዜ አንጻርም የበአሉ ፣ የሃዲስ እና የዳኛቸው ስራዎች በደርግ ዘመን

የተሰሩ ስራዎች ናቸው:: በመሆኑም በአንድ ዘመን የነበረው ፖለቲካዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁነት በሌላ ዘመን የሚከሰትበት መንገድ የተለያየ በመሆኑ ስነጽሁፋዊ ስራዎቹም የዘመኑን መንፈስ ተንተርሰው የሚደረሱ በመሆናቸው የእኔ ጥናት ከዘመን አንጻር በዚህ ዘመን በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ከጭብጥ አንጻር ርዕዮተ ዓለም ፣ መደብ እና ቁሳዊነትን በማንሳት ያላቸውን ተንጸባራቂነት በማሳየት በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ጥናት በኩል የራሱን አስተእዋጽኦ ያበረክታል  በሚል ምክንያት ይህን ጥናት ላጠና ተነሳሁ::

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲካሄድ የሚከተለውን ዓብይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት ነው::

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው የማርክሲዝም  ንድፈ ሃሳባዊ ሥነጽሁፋዊ እሳቤ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ እንዴት እንደተገለጸ/እንደተንጸባረቀ ማሳየት ነው::

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- በልቦለዶቹ ውስጥ ሃይማኖት በምን መልኩ እንደቀረበ መፈተሽ
- በልቦለዶቹ ውስጥ ስርአተ ጾታ ያለውን ሚና መመርመር
- በልቦለዶቹ ውስጥ የመደብ ልዩነት እንዴት እንደተገለጸ መመርመር
- በልቦለዶቹ ውስጥ የተገለጸውን ቁስ አካላዊነት ማብራራት የሚሉት ናቸው::

## 1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በምርምሩ ሂደት ወቅት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል::

1. በልቦለዶቹ ውስጥ የሃይማኖት እሳቤዎች በምን መልኩ ቀርበዋል?
2. በልቦለዶቹ ውስጥ ስርአተ ጾታ ምን ዓይነት ሚና አለው?
3. በልቦለዶቹ ውስጥ የመደብ ልዩነት በምን መልኩ ተገልጿል?
4. በልቦለዶቹ ውስጥ ቁስ አካላዊነት እንዴት ቀርቧል? የሚሉት ናቸው::

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት መካሄዱ ለሥነ ጽሁፍ ተማሪዎች ፣ ለሥነ ጽሁፍ ዝንባሌ ላላቸው ሰዎች(ሥነ ጽሁፍ አጥንተው በተጨማሪ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ላላቸው) ፣ ለሥነጽሁፍ ጥናት እድገትና ይህን ጥናት የማንበብ እድሉን ላገኙ ከሞላ ጎደል ለድርሰት አንባቢዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ።

- ልቦለዶቹ በተጻፉበት ዘመን የነበረውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሁነቶች (በተለይ የመደብ ሁኔታ ፣ የሚንጸባረቀውን ርዕዮተ ዓለም እና የቁሳዊነትን ጽንሰ ሃሳብ) በማሳየት ረገድ የሚጫወተው ሚና አለ።
- ምንም እንኳ ይህ ጥናት የመጀመሪያ ባይሆንም በሂሶች ላይ ተመርኩዞ ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ ትንታኔ መስጠት በሥነ ጽሁፎች ላይ ትኩረታቸውን ላደረጉ እና ለሥነ ጽሁፍ ዝንባሌ ላላቸው ሰዎች በተለይ የማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ማኅበረሰብ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በዚህ ንድፈ ሃሳብ ተመርኩዘው በሥነ ጽሁፍ መልክ የማኅበረሰብን ችግር እና የአኗኗር ሁኔታ እንዴት ማሳየት እንዳለባቸው ግንዛቤ ከመስጠት አንጻር የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል።
- ስለማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ሲወራ ንድፈ ሃሳቡን የተወሳሰበ አድርገው የሚስሉ እና ከፖለቲካዊ ይዘት ጋር ብቻ በማቆራኘት የመሰላቸት ሁኔታ የሚያሳዩ ሰዎች በብዛት ይስተዋላሉ። ይህም ሥነጽሁፎችን በዚህ ንድፈ ሃሳብ የመዳሰስ ሁኔታ ሊቀንስ ይችላል። በመሆኑም ይህ ጥናት የመቀነሱን ክፍተት ለመሙላት አስተዋጽኦ ከማበርከቱ ባሻገር ሌሎች አጥኚዎች ሌሎች የሥነጽሁፍ ስራዎችን በብዛት ይህን ንድፈ ሃሳብ መነሻ በመድረግ እንድያጠኑ አነሳሽ በመሆን ያገለግላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከአለማየሁ ገላጋይ የሥነጽሁፍ ስራዎች መካከል *አጥቢያ* (1999 ዓ.ም) ፣ *በፍቅር ስም(2009 ዓ.ም)* ፣ *ታለ በእውነት ስም* (2011 ዓ.ም) በተሰኙት ረጅም ልቦለዶች ላይ ብቻ የተደረገ ሲሆን የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ መሰረት በማድረግ ንድፈ ሃሳቡ ከሚያጠነጥንባቸው ጉዳዮች መካከልም ርዕዮተ ዓለም (ideology)፣ መደብ(class) እና ቁሳዊነትን (materialism) በመውሰድ በልቦለዶቹ ውስጥ ያላቸውን ተንጸባራቂነት ማሳየት ላይ የተወሰነ ነው። በልቦለዶቹ

ላይ ትንታኔ ሲካሄድ ትኩረት የተደረገው በገጸ ባህሪያቱ ምልልስና በሚነገረው ታሪካቸው ላይ ነው።

## 1.7 የአጠናን ዘዴ

በዚህ ጥናት *አጥቢያ* (1999 *ዓ.ም*) ፤ *በፍቅር ስም*(2009 *ዓ.ም*) እና *ታለ በእውነት ስም* (2011 *ዓ.ም*) በተሰኙት ረጅም ልቦለዶች ላይ የቴክስት ትንተና ተደርጓል። wellek and Austin (1995)እንደሚሉት የቴክስት ትንተና ሲደረግ በዋናነት ትኩረት የሚደረገው በሥነጽሁፋዊ ስራዎች ውስጥ ባሉት ይዘቶች ላይ ነው። በዚህ ጥናት ወቅትም ቴክስቱን በተደጋጋሚ እና በጥልቀት በማንበብ የሚያጠነጥንባቸውን ዋና ዋና ጭብጦች (ርዕዮተ ዓለም ፤ መደብ እና ቁስ አካላዊነት) ነቅሶ በማውጣት ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብን(marksist theory) መታገዪያ መሰረት በማድረግ ልቦለዶቹ ተተንትነው ቀርበዋል። ትንተና ሲካሄድ አገልግሎት ላይ የዋለው ዘዴ ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ነው። ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ረቂቅ እና ውስብስብ የሆኑ ድርጊቶችን በማሳየት ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ለዚህ ጥናት ተመራጭ የመተንተኛ ዘዴ በመሆን አገልግሏል።

ሌላው ለተካሄደው ጥናት አስፈላጊ የሆኑ የአለማየሁ ገላጋይ *"አጥቢያ"* (1999 *ዓ.ም*) ፤ *በፍቅር ስም* (2009 *ዓ.ም*) እና *ታለ በእውነት ስም* (2011 *ዓ.ም*) የተሰኙ ረጅም ልቦለዶቸ ተመርጠዋል። እነዚህን ልቦለዶች ለመምረጥ ተግባር ላይ የዋለው ዘዴ ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው። ይህን ዘዴ መሰረት በማድረግ መጽሐፎቹን ለመምረጥም የሚከተሉት መስፈርቶች በጥቅም ላይ ውለዋል።

- ❖ ልቦለዶቹ ማኅበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ የሆኑ የማኅበረሰብ ጉዳዮችን ስለሚያነሱ እነዚህ ጉዳዮች ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ አንጻር የሚፈከሩ መሆናቸው እና ለጥናቱ ዓላማ መሳካት ጠቃሚ መሆኑ አንደኛው ምክንያት ነው።
- ❖ በሌላ በኩል ከሥነጽሑፍ ጥናት አንጻር በዚህ ንድፈ ሃሳብ የተጠኑ ሥነጽሑፋዊ ስራዎች (የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች) አብዘኻኛዎቹ በደርግ ዘመን የተጻፉ ልቦለዶች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ከጊዜ አንጻር የዚህንም ዘመን (የኢህአዴግ) ሥነጽሑፎች ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ አንጻር ለማየት ታስቦ ነው።
- ❖ የተመረጡት ረጅም ልቦለዶች ከሌሎች የአለማየሁ ገላጋይም ይሁን ሌሎች ደራሲዎች ሥነጽሁፋዊ ስራዎች ለየት የሚያደርገቸው ጉዳይ አለ። ይህም ጉዳይ ከግለሰባዊነት

ይልቅ ማህበረሰብ ላይ ማተኮሩ ነው። በልቦለዱ ውስጥ የሚታዩት ገጸ ባህሪያት የግል ስብእናቸው ፣ የአኗኗር ሁኔታቸው ፣ መልካቸው ፣ የፍቅር ህይወታቸው … ወዘተ የመሳሰሉት የግላዊነት ባህሪያት የሚያስጨንቃቸው አይደሉም። ከራሳቸው ይልቅ ለብዙኃኑ የሚጨነቁ ናቸው። የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብም ከግለሰባዊነት ይልቅ ማህበራዊነት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ጥናቱ የተነሳበትን ግብ ይመታ ዘንድ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ልቦለዱን ለጥናቱ ተመራጭ እንድሆን አድርጎታል።

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ "ማርክሳዊ ንባብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሁፍ በዋናነት አራት ምዕራፎችን የያዘ ነው። ይኸውም ምዕራፍ አንድ መግቢያ ሲሆን የጥናቱ ዳራ ፣የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ዓላማ(ዓብይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች) ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የቴክስት አመራረጥ መስፈርት እና የጥናቱ አደረጃጀት የሚሉትን ንዑሳን ርዕሶች ይዟል።

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት የሚል አብይ ርዕስ ሲይዝ የንድፈ ሃሳብ ቅኝት እና የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ የሚሉ ንዑስ ርዕሶችን አካቷል። ምዕራፍ ሶስት ላይ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብን መታገቢያ በማድረግ በልቦለዶቹ ላይ የተንጸባረቁት ርዕዮተ ዓለም(ideology) ፣ (መደብ(class) እና ቁስ አካላዊነት(materialism)) ትንተና ተደርጎባቸዋል። ምዕራፍ አራት ላይ በምዕራፍ ሶስት ትንታኔ የተደረገባቸው ሃሳቦች ጠቅለል ያለ ሃሳብ(ማጠቃለያ) ቀርቦባቸል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

### 2.1.1 የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ምንነት እና ታሪካዊ ዳራ

የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ በካርል ማርክስና በመጠኑም ቢሆን በፍሪድሪክ ኤንግልስ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ብቅ ያለ የአስተምህሮ አካል ነው፡፡ ይህ የአስተምህሮ አካል ሶስት ተዛማጅ ሃሳቦችን ያቀፈ ነበር፡፡ እነዚህ ተዛማጅ ሃሳቦች የፍልስፍና አንትሮፖሎጂ ፣ የታሪክ ንድፈ ሃሳብና ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካ ጉዳዮች ነበሩ (Tyson, 2006 : 54)፡፡ ካርል ማርክስ የትውልድ ሃረጉ የቡርዧ ቤተሰብ ከሆኑት ጀርመን ነው፡፡ ማርክስ የፖለቲካ ቀማሪና ሶሻሊስት አብዮተኛም ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በ1844 ከፖለቲካል ኢኮኖሚስት ፍሬድሪክ ኢንግልስ ጋር በፓሪስ ተገናኙ፡፡ ሁለቱም ተመሳሳይና ከሌሎች ፍልስፍናዎች ገለልተኛ የሆኑ አመለካከቶች ስለነበራቸው በጋራ በመሆን የኮሚኒስት መርሆችን አወጡ(ማለትም ኮሚኒስት ማኒፌስቶን በጋራ ጻፉ)፡፡ በዚህ ጽሁፋቸውም ውስጥ የኮሚኒስት መምጣትን አበሰሩ፡፡ ሁለቱም ከፖለቲካዊ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ህይወታቸውን በድህነትና በስደት አሳለፉ (Dobei, 2012 : 84)፡፡

በኮሚኒስት ማኒፌስቶ ውስጥ የተብራራው ሃሳብ የመደብ ትግልን እንደ አንቀሳቃሽ ሃይል በመጠቀም እና ሰራተኞቹ ካፒታሊስቶችን በመገልበጥ የኢኮኖሚ ምርትን ወደሚቆጣጠሩበት አብዮት የሚመራ ነበር፡፡በእነዚህ ክስተቶችም የመደብ ልዩነቶች ይጠፋሉ የሚል እምነት ነበራቸው፡፡

የማርክስ ንድፈ ሃሳብ በዋናነት መደብ አልባ ህብረተሰብ መፍጠር አለብን የሚል ነበር፡፡ ማህበራዊ መደቦቹም መለያየት የሚመጡት ባለው የምርት ስርዓትና የማምረቻ እቃዎች በካፒታሊስቶች መያዝ ነው ብሎ ያምናል፡፡ በዚህም የታችኛው መደብ ወይም እንደ ማርክስ አጠራር ፕሮሌታሪያት የሚባለው የማህበረሰብ ክፍል ጭቆና ወይም ብዝበዛ ይደርስበታል የሚል ነው፡፡ በዚህም ሂደት የኢኮኖሚውን አካሄድ መቀየር እንዳለበት ያምናሉ፡፡ ስለዚህ የመደብ ትግልን በማጧጧፍ ሰራተኞች ካፒታሊስቶችን ወደመገልበጥ እንዲደርሱ የሚያደርጉ አስተምህሮዎችን ያስፋፉ ነበር፡፡ ይህ ሃሳብ Dobie (2012 :84) Marx and Engels(1848)ን ጠቅሶ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡፡

የመደብ ትግል ታሪክን እንደ አንቀሳቃሽ ኃይል በመለየት እና ሰራተኞች ካፒታሊስቶችን እንዲገለብጧቸው በማድረግ ፣ የኢኮኖሚ ምርትን ወደ ተቆጣጠሩበት እና የግል ንብረትን ወደሚያስወግድ አብዮት ይመራል የሚል ግምት ነበራቸው ። በዚህም ሂደት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲሰራጭ የግል ንብረቶችን ለመንግስት በመስጠት የመደብ ልዩነቶች እንድጠፉ ማድረግ ይቻላል።

### 2.1.2 ማርክሲዝምና ሥነ ጽሁፍ (Marxism and Literature)

በርግጥ ማርክስ ምንም ዓይነት የሥነ ጽሁፍ ስራ እንዳልሰራ Barry (2002 : 107 ) አስቀምጧል። ይሁን እንጅ ማርክሲዝም በአካባቢያችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ፣ በተፈጥሯዊው ዓለምና በምንኖርበት ማህበረሰብ ላይ በመመርኮዝ ዓለምን ለመተርጎም የሞከረ የቁሳዊ ፍልስፍና አካል ነው። ይህም ከሃሳባዊ ፍልስፍና ጋር የሚቃረን ነው። በአንደኛው መንገድ ከፊቱ የመጡ አጠቃላይ ፍልስፍናዎችን በመጣስ የሰዎችን አስተሳሰብ ወደ ተቃራኒ አስተሳሰብ ለመቀየር ሞክሮ ነበር።

Barry (2002 : 107) እንዳስቀመጠው ምንም እንኳ ማርክሲዝም አንድ የስነ-ጽሁፍ ትንተና ዘዴ ባይሆንም መርሆቹ ግን በስነ-ጽሁፍ ውስጥ ተተግብረዋል። ስነ-ጽሁፍ አንዳንድ ጊዜ እንደፍሬያማ ወሳኝ የውይይት መድረክ ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘበት በሌላ ጊዜ ደግሞ የፓርቲ ርዕዮተ ዓለምን የሚያራምድ ከሆነ እንደስጋት በሚታይበት ሩሲያ ስነ-ጽሁፍ በማርክስና ኤንግለስ ከተቀመጡት የፍልስፍና መርሆች ጋር የተቆራኘ ነበር።

በማርክሲዝም ውስጥ ስለ ሥነ-ጽሁፍ ሲነሳ የተለያዩ አመለካከቶች አብረው ይነሳሉ። Eagleton (2003 : 5) በበኩሉ "ኪነ ጥበብ ለማርክሲዝም የኅብረተሰቡ ልዕለ መዋቅር አካል እና የርዕዮተ ዓለም ማንጸባረቂያ ነው።" ይላል። በሌላ በኩል Eagleton(2003 : 5) አልቱሰር "ኪነ-ጥበብ ወደ ርዕዮተ ዓለም ሊቀየር አይችልም። ይልቁንስ ሁለቱ ግንኙነት አላቸው።" ሲል እንደሚከራከር ይናገራል። Lukacs ሥነ ጽሁፍ የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊና የሚያንጸባርቅ ነው ቢልም Althusser ሂደቱ በሌላ መንገድ ሊሆን እንደሚችል ይናገራል። በአጭሩ ኪነጥበብ እና ሥነ ጽሁፍ በህብረተሰብ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ ይላል( Eagleton, 2003 : 5)። ይህም ማለት ከፍተኛው መደብ ርዕዮተ ዓለምን ስለሚቆጣጠር የሰራተኛውን ክፍል የከፍተኛው መደብ ርዕዮተ ዓለም በተዛባ መንገድ እንዲቀበል ስለሚደርገው ነው። በዚህም ሥነ ጽሁፍ በማህበራዊ ግልጋሎቱ እና በጥበባዊነት ውጤቱ መካከል ያለው ግንኙነት ይፈርሳል ማለት ነው። አልቱሰር ርዕዮተ አለምና ኪነ-ጥበብ ያላቸውን ግንኙነት ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡-

ርዕዮተ ዓለም ሰዎች ትክክለኛውን ዓለም የሚለማመዱበትንና በምናባቸው የሚስሉትን መንገድ ይመለከታል፡፡እነዚህ ልምዶች ግን የሥነ-ጽሁፍ አካላት ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ኪነ-ጥበብ እነዚህን ተሞክሮዎች ሊያንጸባርቁ ይችላሉ፡፡ ይሄ በርዕዮተ ዓለም ውስጥ ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን ማራቅም ይቻላል (Eagleton, 2003: 16)፡፡

በሌላ በኩል Eagleton (2007:41) እንዳስቀመጠው ሥነ ጽሁፍ የማህበረሰቡን እውነት እንደሚያስረዳ ነው፡፡በዚህም ተጨባጭ የሶሻሊስት እውነታን መቅረጽ ይቻላል የሚል እምነት አላቸው፡፡

Althusserም በበኩሉ "እውቀት እውቀት የሚሆነው ሳይነሳዊ ሲሆን ነው" ይላል፡፡ካፒታሊዝም አንድ የእውቀት ዘርፍ ነው፡፡ኪን ጥበብና ሳይነስም የተለያዩ ነገሮች አይደሉም ፤ ይልቁንም ተመሳሳይ ነገሮችን በተለያየ መንገድ እንድናይ ይረዱናል ይላል፡፡ ይህም ሳይንስ የአንድን ሁኔታ ጽንሰ ሃሳባዊ እውቀት ሲሰጠን ኪነ ጥበብ ደግሞ የሁኔታዎችን ልምድ ይሰጠናል፡፡ ይህም ከርዕዮተ ዓለም ጋር የሚመጣጠን ግንዛቤ ነው፡፡ ርዕዮተ ዓለምም አንድን ግንዛቤ እንድናይ የሚስችል ሳይንሳዊ እውቀት ነው(Eagleton, 2014 :17)ይላል፡፡ስለሆነም የማህበረሰቡን እውነታዎች የሚያነጸባርቅና ተለምዷዊ ማህበራዊ ልማትን የሚገልጽ በመሆኑ ሥነ ጽሁፍ የተራቀቀ የውበት ቴክኒኮችና ልቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

Tyson (2006 : 54) "ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ የተለያዩ የጥበብ ሥራዎች ሥነ ፅሁፍ፣ ፊልም፣ ቲያትርና ግጥም ወዘተ ሊፈተሹበት የሚችል ሲሆን በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለው ተጨባጭ የአቅም ግንኙነት በሥራዎች ውስጥ እንዴት ተንፀባርቋል የሚለውም ይዳስስበታል" ትላለች፡፡

ታይሰን እንደገለጸችው ሥነ ጽሁፍ የማህበረሰቡ የህይወት ነጸብራቅ እንደመሆኑም የዚያን የህብረተሰብ የአኗኗር ሁኔታ እንዴት በሥነ ጽሁፉ ውስጥ እንደተንጸባረቀ ልንመዝንበት የምንችልበት ንድፈ ሃሳብ መሆኑን ነው፡፡ በመግቢያው ላይም ለመግለጽ እንደተሞከረው የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች በፈለቁ ቁጥር የተለያዩ የሥነጽሑፍ መተቻ ወይም ሂስ ማድረጊያ መንገዶችም እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ መምጣት ጋር ተያይዞ ማርክሳዊ ሂስም ዘልቋል ማለት ነው፡፡ ማርክሳዊ ሂስ ምን እንደሆነ እና ምን ዓይነት ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ Tyson (2006 : 66) እንደሚከተለው አስቀምጣለች፡፡

ማርክሳዊ ሂስ በሥነጽሑፍ ውስጥ የመደብ ልዩነት ፣ በኢኮኖሚና በሌሎችም የፖለቲካ ልዩነቶች የሚኖረውን አንድምታ ይፈትሻል፡፡ ማርክሳዊያን ሥነጽሑፍን በጊዜ ገደብ

ውስጥ በኪናዊ እውቀት አማካኝነት ንቁ ተሳትፎ ሳይደረግበት የሚፈጠር አይደለም ይላሉ። ነገር ግን በአንድ ባህል በተወሰነ ጊዜና ቦታ ውስጥ የሚታይ የማህበረሰቡ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊና የአመለካከት ሁኔታ ደራሲው አስቦ ያድርገውም አያድርገውም የሚነጸባረቅበት ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ፍጡር ስለሆነና የራሱ የሆነ አመለካከት ያለው በመሆኑ ደራሲውም የሥነጽሑፍ ሥራውን ከዚህ ውጭ ማድረግ አይችልም።

ስለዚህ የሚጻፈው ሥነጽሑፍ አንድም የህብረተሰቡ የኑሮ አካል ነው በሌላ በኩልም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የታመቀ ጭቆና እንደማቀጣጠያነት የሚያገለግል እራሱ የትግሉ ማንቀሳቀሻ ሃይል በመሆን ያገለግላል ማለት ነው። ስለዚህ ምንም እንኳ ማርክስና ኤንግልስ የሥነጽሑፍ ስራዎችን ባይጽፉ በተለያዩ ደራሲዎች የሚጻፉትን ሥነጽሑፋዊ ስራዎች የትግሉ ቀስቃሽና የርዕዮተ ዓለም ማንጸባረቂያ ናቸው የሚለው አመለካከት በመንጸባረቅ ንድፈ ሃሳቡን በቀጥታ ከሥነጽሁፍ ጋር በማገናኘት የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን የሚያትቱ ሥነጽሁፋዊ ስራዎች እንዲበራከቱ መንገድ ከፍተዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያዩ የጊዜ ሂደቶች የሚታተሙት የተለያዩ የሥነጽሑፍ ስራዎች አንባቢን ወደ ትግልና አመጽ የሚገፋፉም እንደነበሩ የሚታወስ ነው።ስለዚህ የማርክስና የሥነጽሑፍም ዋነኛው ግንኙነታቸው ሥነጽሑፍ የልዕለ መዋቅሩን ሥርዓት የሚያሳይና የርዕዮተ ዓለም ማንጸባረቂያ ነው ማለታቸው ነው።

### 2.1.3 ሥነ ጽሁፍና ላዕላይ መዋቅር (Literature and Superstructure )

እንደ Castel (2007) አገላለጽ መሰረት የማርክሲዝም ማኅበራዊ ጽንሰ ሃሳብ በላዕላይ መዋቅር ንድፍ ይጀምራል። ላዕላይ መዋቅሩም የሚያመለክተው የምርት ሁነቶችን እንዲሁም በምርት ሁነቶች የተፈጠሩትን መደቦችና የመደብ ግንኙነቶችን ነው። በዚያም የገዥው መደብ ልዩ ርዕዮተ ዓለምን የሚያራምዱና የሚያንጹ ማኅበራዊና ባህላዊ ተቋማት ይገነባሉ። የሚንጸባረቀውም ርዕዮተ ዓለም የማምረቻ መሳሪያዎችን ከሚቆጣጠረው የገዥው መደብ ሃሳቦችና እምነቶች የተቆራኘ ነው። ላዕላይ መዋቅር የምንለው ይህ ስርዓት የሚራመድበትን ሂደት ነው። ላዕላይ መዋቅር ከሥነ ጽሁፍ ጋር ያለውን ግንኙነት ደግሞ Eglaton (2002 :5) እንደሚከተለው አስቀምጧል። “ኪነ ጥበብ ለማርክሲዝም የኅብረተሰቡ ላዕላይ-መዋቅር እና የኅብረተሰብ ርዕዮተ ዓለም አካል ነው።” እንደዚህ ባለ ውስብስብ የማኅበራዊ ግንዛቤ መዋቅር ውስጥ አንድ ማኅበራዊ ክፍል በሌላው ላይ ሥልጣን ያለበት ሁኔታ መኖሩንና ይህ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደታየ የሚያረጋግጥ ነው።

ስለዚህ ሥነ ጽሁፍ የላዕላይ መዋቅሩ አካል በመሆን የገኘውን ሃሳብ ፣ አመለካከት ፣ የአመራር ሁኔታ ፣ ህግ እና ስርዓቶችን ሳይቀር በማራመድና በማንጸባረቅ ያገለግላል ማለት ነው።

## 2.1.4 ሥነ ጽሁፍና ርዕዮተ ዓለም (Literature and Ideology)

ርዕዩተ ዓለም በማርክሲስቶች መሠረት የሚገለጸው በኅብረተሰብ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ክፍሎች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ፣ በኅብረተሰቡ የምርት ሁነቶች ምክንያት የመጡ ክፍሎችን በማመንጨት ነው ። ርዕዮተ ዓለም አዎንታዊ ሊሆን ይችላል ፣ ይህም ህዝቦችን ወደ ተሻለ ዓለም ይመራቸዋል ፤ ወይም ደግሞ የአፋኝ ስርዓት ፍላጎቶችን የሚያራምድ አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ይህንን ሃሳብ በማጠናከር ርዕዮተ ዓለምን በአሉታዊ እና በአወንታዊ መንገድ መመልከት እንዳለብን Tyson (2006 :56) እንደሚከተለው አስቀምጣዋለች።

> ለማርክሲዝም ርዕዮተ ዓለም የእምነት ስርዓት ነው። ሁሉም የእምነት ስርዓቶች የባህል ውጤቶች ናቸው። ለምሳሌ ካፒታሊዝም ፣ ኮሚኒዝም ፣ ማርክሲዝም ፣ ፓትሪያርኪዝም ፣ ሃይማኖት ፣ ሥነ ምግባራዊ ሥርዓቶች ፣ ሰብአዊነት ፣ አካባቢያዊነት ፣ ኮከብ ቆጠራ እና ካራቴ የመሳሰሉት ሁሉ ርዕዮተ ዓለም ናቸው። ተፈጥሮ በሳይንስ ህግ መሰረት ትመራለች የሚለው እንኳን ርዕዮተ ዓለም ነው። እኛ የምናስበው ማንኛውም ልምድ ወይም የጥናት መስክ የርዕዮተ ዓለም ክፍል ነው። ሁሉም ርዕዮተ ዓለም በእኩል ደረጃ ጠቃሚ ወይም ተፈላጊ አይደለም። የማይፈለጉ አፋኝ ርዕዮተ ዓለምን የሚያራምዱ አሉ።

በማርክሲስቶች አስተሳሰብ ግለሰባዊነት ከአፋኝ ርዕዮተ ዓለም ይቆጠራል። የግለሰቦቹም ፍላጎት ከ "እኛ" ይልቅ "እኔ" ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የተዛባ ነው (Tyson,2006: 60)። ይህ ግለሰባዊነት ራስን ብቻ ትክክልና የሁሉ ነገር አዛዥ/ተጠቃሚ የማድረግ ልምድን ስለሚያደብር የሌሎችን ፍላጎትና ጥቀም በመጋፋት ተጨቋኝ እንዲሆኑ ያደርጋል።ማርክስ እንደነዚህ ያሉ አፋኝ ርዕዮተ ዓለሞችን ማስወገድ አለብን ብሎ ያምናል።

ከልዕለ መዋቅሩም ጋር ተያይዞ ርዕዮተ ዓለም ይነሳል። ርዕዮተ አለሙም የማኅበረሰቡን ችግር የሚመለከትና የሚፈታ ሳይሆን የላይኛውን መደብ የሚያንጸባርቅ ነው። Eglaton (2002 : 12) እንደገለጸው "የርዕዮተ ዓለም ተግባር እንዲሁ በኅብረተሰቡ ውስጥ የገዢ መደብ ስልጣንን ህጋዊ ማድረግ ነው። በመጨረሻ ግን የአንድ ኅብረተሰብ የበላይ ሀሳቦች የገዢ መደብ ሀሳቦች ሆነው ይደመደማሉ።" ስለዚህ አንድን ኅብረተሰብ ወክለው የሚንጸባረቁ ርዕዮተ ዓለሞች ቢኖሩ እንኳን መደምደሚያቸው የልዕለ መዋቅሩን ሃሳብ ማጉላት ይሆናል።

በሌላ በኩል ከዚህ በላይ ከተነሱት ሃሳቦች ተቃራኒ ሃሳብም ይነሳል፡፡ ይህም ርዕዮተ ዓለም የገዥውን መደብ ሃሳብ ብቻ የሚያራምድ ሳይሆን የአንድን ማኅበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ ፣ ባህል ፣ ወግ እና ልማድ ፣ ስሜቱን ፣ እምነቱን ፣ በእምነቱ ላይ ያለውን ቁርጠኝነት ፣ ፍቅሩን ጥላቻውን ... ማንጸባረቂያ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ Castel (2007 :111) Raymond Williams(1977)ን ጠቅሶ እንዳስቀመጠው ርዕዮተ ዓለም ውስብስብ እና ሁለገብ የሆነ ክስተት እንደሆነ እና "የአንድ የተወሰነ ክፍል ወይም ቡድን ማኅበረሰቦች ያላቸው ባህሪ እና የእምነት ስርዓት" ብቻ ሳይሆን "የእውነተኛ አስተሳሰብ ስርዓት" ሊያመለክት እንደሚችል ልብ ማለት እንደሚገባ ነው፡፡

በሌላ በኩል Castle (2007) ; Althutsser (1971)ጠቅሶ እንዳሥቀመጠው አልቱሰር "ሰዎች ርዕዮተ ዓለምን እንደሚፈጥሩ ሁሉ ርዕዮተ ዓለምም ለግለሰቦች የዓለም እውነታዎችን በመገንባት የራስ ምስላቸውን የሚፈጥር ነው፡፡" ይላል፡፡ በተጨማሪም ርዕዮተ ዓለም የግለሰቦችን ምናባዊ ሃሳቦችና እውነተኛው የኑሮ ሁኔታ ያላቸውን ዝምድና እና ውክልና ይመለከታል(Althusser, 1971: 181)፡፡ ለምሳሌ ሃይማኖታዊ ፣ ስነ-ምግባራዊ ፣ ህጋዊ ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች አስተሳሰቦችን መጥራት ይቻላል፡፡ ሌሎችንም የዓለም አመለካከቶች ብንመለከት በእኛ ልማድ እያንዳንዱን ርዕዮተ ዓለም እውነተኛ ናቸው ብለን አምነን የተቀበልናቸው ናቸው፡፡ በአመዛኙ ግን ምናባዊ ናቸው ከእውነታው ጋር አይዛመዱም(Althusser,1971: 182)፡፡ አልቱሰር እንደሚለው ርዕዮተ ዓለሞች ሁሉ ትክክል/እውነት አይደሉም ምናባዊ የሆኑም እንዳሉ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሃይማኖታዊ ርዮተ ዓለም የተለያዩ ትርጓሜዎች ይሰጡት እንደነበር (Althusser,1971 :182)ይናገራል፡፡ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን "God is an imaginary representation of the real King" "እግዚአብሔር ምናባዊ እና የእውነተኛው ንጉስ ወኪል ነው" የሚል የጋራ አመለካከት ነበራቸው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ርዕዮተ ዓለም ግልሰቦች ፣ አንድ የህብረተሰብ ክፍል ወይም መደብ ፣ አንድ ቡድን ወይም ድርጅት እምነታቸውን እና አመለካከታቸውን የሚገልጹበት የሃሳብ ምጥቀት ያለው አላማ መድብል ሲሆን በተለይም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፖሊሲዎችን እና ንድፈ ሃሳቦችን ከማህበረሰባዊ አንድምታቸውና ባህላዊ ገጽታቸው ጋር በማካተት ተዋናዩ ህብረተሰብ የሚገኝበትን ታሪካዊ ሁኔታና ወቅትም የገዞ አቅጣጫ አመልካች ነው፡፡

### 2.1.5 ቁስ አካላዊነት (Materialism)

የማርክስ ታዋቂው ርዕዮተ ዓለም ቁስ አካላዊነት ሲሆን ሃይማኖት ፣ ስነ-ምግባርና ማህበራዊ መዋቅሮች በሙሉ መሰረታቸው ኢኮኖሚ ነው ብሎ ያምን ነበር፡፡ ቁስ አካልነት ዋና የፍልስፍና አይነት ሲሆን ዓለም የተሰራችው ከቁሳዊነት ብቻ እና ባህሪዋም የቁስ አካል ዓይነት ነው የሚል ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ማናቸውም የመንፈሳዊም ሆነ የሃሳብ ክስተቶች ከቁስ አካል ጋር የተገናኙና እነሱን ከሚገዙ ህግጋት የሚመዘዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ብቸኛው የዓለም ነባራዊ ክፍል ከሃሳብ ነጻ ህልውና ያለው ቁስ አካል ነው፡፡ በመሆኑም ቁስ አካላዊነት የሐሳባዊነት ተቃራኒ ነው፡፡

በዚህም ምክንያት "የቁስ አካልነት አጠቃላይ ፍቺና ሚና የሚገለጸው ከሃሳባዊነት ጋር ካለው ልዩነትና ትግል አንጻር ነው፡፡ ማንኛውም የአስተሳሰብ ሆነ የተግባር ጥያቄ ተቃራኒ በሆኑ ሃሳባዊና ቁስ አካላዊ መልሶች ይተረጎማል፡፡ በመሆኑም የቁስአካልነት ምንነት የሚገለጸው ከሃሳባዊነት በሚለዩት ጠባያት ነው" (ማርክሲዝም ሊኒኒንዝም መዝገበ ቃላት ፤ 1987 ፣ 195) ፡፡ ከዚህም አንጻር የቁሳዊነትን ምንነት ለመረዳት ከሃሳባዊነት ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት እያነጻጸሩ ማየት ያስፈልጋል፡፡

Dobei (2012 ፡ 90) እንዳስቀመጠው ማርክስ የምንኖርባት ዓለም የተገነባችው በቁሳዊነት እንጅ በሃሳባዊነት እንዳልሆነ ፤ እኛነታችንም ቁሳዊነት እንጅ ሃሳባዊነት አለመሆኑን ፤ ማንነታችንም የሚቀረጸው ከቁስ እንጅ ከፍልስፍና ወይም ከሃይማኖት አለመሆኑን ፣ አፈጣጠራችንም ቢሆን የራሳችን ባህላዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ፈጠራዎች እንጅ የመለኮት ዲዛይን አለመሆናችንን የሚያሳይ እምነት እንዳለው ነው፡፡

Dobei (2012) ከዚህ ሃሳብ ጋር አያይዞ "ማርክስ እራሳችንን ለመረዳት በየቀኑ የምንኖርበትን ተጨባጭና ታዛቢ የሆነውን ዓለም መመልከት አለብን" የሚል አመለካከት እንዳለው ይገልጻል፡፡ ቁሳዊው ዓለም እውነታውን ያሳየናል ፡፡ ድርጊቶቻችን ሁሉ እርስ በእርስ እንዲዛመዱ በማድረግ ሰዎች በማህበራዊ ቡድኖች ውስጥ እንደሚኖሩ ያሳያል፡፡ በማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ክፍሎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በመመርመር እና ላዕላይ-መዋቅሩን በመተንተን ስለራሳችን እና ስለማህበረሰባችን ግንዛቤን ማግኘት እንችላለን ፡፡ ሆኖም ሃሳባዊነት ከሁሉ አስቀድሞ ሃሳብን የሁሉ ነገር መሰረት ሲያደርግ ቁስ አካላዊነት ደግሞ ቁስ አካልን የሁሉ ነገር መነሻ አድርጎ ይወስዳል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል Castel (2007 :112)በማርክስ እይታ ሰው ማህብራዊ ፍጡር ነው፡፡ማህበራዊ ፍጡር የሚያደርገውም የሚኖረው የምርት ግንኙነት ነው ይላል፡፡ ሰዎች በማህበራዊ የምርት ህይወታቸው ውስጥ ያለው ግንኙነታቸው ከምርት እና ከቁሳዊ ሃይሎች ጋር የተዛመደ ነው፡፡ የዚህ የምርት ግንኑነት የህግና የኢኮኖሚ አወቃቀር ፣ ህጋዊና ፖለቲካዊ ላዕላይ መዋቅሩ የሚወጣበትና ቁሳዊ ህይወት ከትክክለኛው ማህበራዊ ንቃተ ህሊና ጋር የሚያዛምድ ነው፡፡ የእነዚህ መሰል ሁኔታዎች ንቃተ ህሊና የሚወሰነው በሰዎች አይደለም፡፡ በተቃራኒው ሰው የእነዚህ ማህበራዊ ፍጡር ይሆናል (Castel; 2007 :112)፡፡

2.1.6 መደብ (class)

መደብ ለሚለው ቃል የተለያዩ ጸሃፍት የየራሳቸውን ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993 ፣ 64) ብናይ እንዲህ ይላል፡፡

> መደብ... በአንድ በተወሰነ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ኅብረተሰብ ውስጥ በማምረት ተግባር ላይ ባለው ሚና ፣ ከማምረቻ መሳሪያ ጋር ባለው ግንኙነት ፣ ምርትን በመከፋፈል ረገድ ባለው ድርሻ እና ድርሻውን በሚያገኝበት ዘዴ አንዱ ከሌላው የሚለይበት የሰዎች ቡድን ወይም ክፍፍል ፤ የላብ አደሩ መደብ ነው ይላል፡፡

በዚህ አገባቡም ሰዎች በኢኮኖሚ ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ እና በማኅበራዊ ጉዳዮች የሚፈጥሩትን የመደብ ልዩነት የሚመለከት ነው፡፡ ይህንንም ማርክሲዝም ሊኒኒዝም መዝገበ ቃላት እንዲህ ያስረዳል፡፡

> መደብ የኅብረተሰቡን ማህበራዊ ክፍፍል የሚያመለክት ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ሰዎች በታሪክ በተወሰነ የማህበራዊ ምርት ስርዓት ውስጥ በሚይዙት ስፍራ ከምርት መሳሪያዎች ጋር(በአብዛኛው በህግ የሚወሰንና የሚቀረጽ) ባላቸው ግንኙነት በማህበራዊ የስራ አደረጃጀት ውስጥ በሚጫወቱት ሚናና ከዚህም የተነሳ በማህበራዊ ምርት በሚያገኙት ድርሻና መጠን በተለያዩ መደቦች ይከፋፈላሉ (የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት ፤ 1978 ፣ 65)፡፡

እንደ ማርክስ መደቦች የሰዎች ስብስብ ቢሆኑም ማናቸውም የሰዎች ስብስብ ግን መደብ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ሴቶች፣ ወጣቶች ፣ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ....ወዘተ በርካታ አባላት ያሏቸው ቡድኖች ቢሆኑም መደቦች ግን አይደሉም፡፡ ምክንያቱም አንዳንዶቹ ተፈጥሯዊ መሰረት ያላቸው በመሆኑ እና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ደግሞ ለሰዎች እኩል አለመሆን ምክንያት ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ማህበራዊ መሰረት ቢኖራቸውም እራሳቸውም ወሳኝ በሆነው ኢኮኖሚያዊ ልዩነት የተነሳ በመደብ የተከፋፈሉ በመሆናቸው ነው፡፡ መደቦች

የሚፈጠሩት ሰዎች የወል ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም እንዳላቸው ሲያውቁና እነዚህን ጥቅሞቻቸውንም ከሌሎች ሰዎች ጥቅሞች የተለዩ ብቻ ሳይሆኑ ተጻራሪ እንደሆኑ ተረድተው የወል ጥቅማቸውን በጋራ ለማስከበር ሲነሱ ነው። ስለሆነም የወል ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን መረዳትና የፖለቲካዊ ድርጅታቸውን መመስረት በርሱም መመራት የጎሊና ሁኔታን መሟላት ያሳያል። የመደቦች በኢኮኖሚ ጥቅም መለያየት በፖለቲካ፣ በርዕዮተ ዓለም፣ በፍልስፍና፣ በባህል ወዘተ... ዘርፎች እንዲታገሉ ያደርጋቸዋል።

> መደቦች ሁሌም የነበሩና የሚኖሩ ሳይሆኑ በማኀበራዊ የምርት ዕድገት ሂደት ውስጥ የተከሰቱና የሚጠፉም ናቸው። የመደቦች መከሰት መንስኤ የማህበራዊ የስራ ክፍፍል ማደግና የማምረቻ መሳሪያዎች በግል መያዝ ነው። የመደቦች መፈጠር ኀብረተሰቡን በገዥና በተገዥ፣ በበዝባዥና በተበዝባዥ ኃይሎች እንዲከፋፈል ያደርጋል። ፀረ ብዝበዛ አቋም ያለው የወዛደሩ መደብ በሶሺያሊስት አብዮት አማካኝነት ሥልጣን ሲጨብጥ በኀብረተሰቡ ውስጥ የሚያታየውን መደባዊ ክፍፍል እየደመሰሰው ይሄዳል(ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገብ ቃላት ፤1987 ፣ 66)።

ለዚህም ነው ማርክስ የመደብ ትግሉን በማጧጧፍ ሶሻሊስት ማህበረሰብ መፍጠርና መደብ አልባ ህብረተሰብ መፈጠር አለበት የሚለው። በመደብ በተከፋፈለ ኀብረተሰብ ውስጥ በአንድ ወቅት ሰፍኖ የሚገኘው ስልተ ምርት ከሚፈጥራቸው መሰረታዊ መደቦች ሌላ መሰረታዊ ያልሆኑም መደቦች ሊገኙ ይችላሉ። በቡርዧው ኀብረተሰብ ውስጥ የገበሬው መደብ፣ በፊውዳሉ ኀብረተሰብ ውስጥ የቡርዧውን መደብ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ከነዚህ በተጨማሪ በአንድ ኀብረተሰብ ውስጥ መደብ ያልሆኑ ነገር ግን የወል ባህሪ ያላቸው እንደ ተማሪና እንደ አስተማሪ ያሉ ማህበራዊ ቡድኖች ይገኛሉ። በሌላም በኩል ደግሞ የአንድ መደብ አባላት የሆኑ ነገር ግን ከአጠቃላዩ የመደብ ባህሪና ጥቅም ባሻገር እርስ በእርሳቸው የሚለያዩበት ባህሪና ጥቅም ያላቸው የሞኖፖል ቡርዧ ፣ የኢንዱስትሪ ቡርዧ፣ የንግድ ቡርዧ ወዘተ... የሚባሉ ክፍሎች ይገኛሉ። በኢንዱስትሪም ውስጥ የኢንዱስትሪ ወዛደር ፣ በገበሬው ውስጥ ደግሞ ከፍተኛው፣ መካከለኛውና ዝቅተኛው ገበሬ የሚባሉ ክፍሎች ይገኛሉ። ስለዚህ ይላል ማርክስም “መደብ የኢኮኖሚ ልዩነት መገለጫ ነው”( Marks, and Engles, 1848)።

ከተሰጡት ማብራሪያዎች መረዳት የሚቻለው መደብ ሃብታም እና ድሃ ወይም ዝቅተኛው የማህበረሰብ ክፍልና ከፍተኛው የማህበረሰብ ክፍል አልያም ባለ እርስቱንና ጭሰኛውን የሚመለከት ነው ማለት ነው። እነዚህ ልዩነቶች የሚፈጠሩት ደግሞ እንደማርክስ እምነት

ስርዓቱ ስራ አጦችን ስለሚያስፋፋ እና ካፒታሊስቶች ለሰራተኛው መደብ መክፈል የሚገባቸውን ደመወዝ ስለማይከፍሉ ነው ይላል። ይህንንም ሃሳብ ታይሰን እንዲህ ስትል ትገልጸዋለች።

> ማርክስ ካፒታሊስቶች ሃብታም የሚሆኑት ለሰራተኛው መደብ መክፈል የሚገባቸውን ደመወዝ በትርፍ መልክ እየበዘበዙ ገንዘብ በማካበት መሆኑን ይገልጻል። እንደ ማርክስ አስተሳሰብ በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ሰራተኞች የሚያገኙት ደመወዝ በምርት ተግባር ወቅት ለስራ ከሚያፈሱት ሃይል ዋጋ በታች ነው። ይህ የሚሆነውም ስርዓቱ ስራ አጥነትን ስለሚቀፈቅፍ በአነስተኛ ደመወዝ ብዛት ያለው የሰው ሃይል የግድ ስለሚፈጥር ነው የሚለውን ማርክሳዊ ርዕዮት ነው። በዚህም መሰረት በማርክሲዝም ትርፍ ማለት ለሰራተኛው ያልተከፈለ ደመወዝ ወይም ተረፈ እሴት(ሰርፐለስ ቫልዩ) ነው ይላል። ስለዚህ እንዲህ ያለውን ያልተመጣጠነ የትርፍ ክፍፍል ማስቆም የሚቻለው የመደብ ትግሉን ማጧጧፍ እና የካፒታልስቱን ስርዓት በመነቅነቅ ኮሚዩኒስታዊ ስርዓትን መመስረት ሲቻል ነው ይላል ማርክስ (Tyson, 2006 : 54)።

ከላይ የተብራራው ሃሳብ የሚያመለክተው መደብ በኢኮኖሚ ልዩነት የሚመጣ መሆኑንና ይህ የመደብ ልዩነት ደግሞ በኅብረሰቦች መካከል በዝባዥና ተበዝባዥ ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ ፣ ጌታና አገልጋይ ... ወዘተ የመሳሰሉትን ልዩነቶች አምጥቷል። ይህ ልዩነት ደግሞ የተወሰነውን የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የተወሰነውን ደግሞ ተጎጅ እያደረገ በመሆኑ በመደቦች መካከል አለመስማማት ወይም መጋጨት ሊከሰት ይችላል። ይህም ግጭት እያደገ ሲመጣ የመደብ ትግል ይሆናል። የታችኛው ክፍልም ከጭቆናው ለመላቀቅ በላይኛው ክፍል ላይ ያምጻል። ይህም የመደብ ትግል መከሰትን ያሳያል።

Marks and Engles(1848) መደብ የኢኮኖሚ ልዩነት መገለጫ እንደሆነ እና በእነዚህ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ መደቦች ውስጥ ያሉ ልዩነቶች ሰዎችን በሃይማኖት ፣ በዘር ፣ በጎሳ ወይም በጾታ እንደሚከፋፍሉ ይናገራል። እነዚህ ጉዳዮችን መሰረት አድርጎ ሰዎች “ያላቸው” እና “የሌላቸው” በማለት ይመደባሉ(Tyson,2006 : 71)። በኢኮኖሚ ልዩነት የተነሳ የተፈጠረው የመደብ ልዩነት ማህበረሰቦችን አንዱን አዛዥ ሌላውን ደግሞ ታዛዥ ፤ አንዱን በዝባዥ ሌላውን ተበዝባዥ በማድረግ የበላይና የበታችነትን የሚፈጥር ነው። ይህም ለመደብ ትግል ያነሳሳል።

### 2.1.6.1 **ማርክሲዝምና የመደብ ትግል** (marxism and class struggle)

የመደብ ትግል ጥቅማቸው የማይጣጣም ወይም ተቃራኒ የሆኑ መደቦች የሚያደርጉትን ትግል የሚገልጽ ጽንሰ ሃሳብ ነው። ከባሪያ አሳዳሪው ስርዓት ጀምሮ የኅብረተሰብ ታሪክ የመደብ ትግል

ታሪክ ነው። በማርክሲዝም ሊኒኒዝም አመለካከት ኅብረተሰብ ተቃራኒ በሆኑ መደቦች መከፋፈሉና የመደቦች ትግል ማካሄዱ የዕድገቱ መሰረትና አራማጅ ኃይል ሆኖ ቆይቷል። የዚህ አመለካከት ሳይንሳዊነትም የሚረጋገጠው ትግሉ ከቡርዧ ኅብረተሰብ ላይ ሲደርስ በማይቀር ሁኔታ ወደ ወዛደር የበላይ ገዥነት በማምረት መደቦችን የሚያጠፋ ኅብረተሰብ እንደሚመሰረት ማስረዳቱ ነው።ይህም ማለት መደቦችን ያመጣ ታሪካዊ ሁኔታ መደቦች ሚናቸውን ሲያጠናቅቁ መልሶ ያስወግዳቸዋል (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት ፣1987 ፣ 67-68)።

ከላይ ከተገለጸው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የመደብ ትግል ዋነኛ ዓላማው የመደብ ትግሉን አጧጡፎ ዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል ወይም ወዛደሩ የበላይነት አግኝቶ አዲስ ሶሻሊስታዊ ስርዓትን መገንባት ነው። በሶሻሊስት ስርዓቱም መደብ የሚለው ነገር ይጠፋና ኅብረተሰቦች እኩል ይሆናሉ የሚል አንድምታ አለው።

Dobie (2012: 92) ማርክስ ስለመደብ ግጭት ያለውን አመለካከት እንዲህ ሲል አስቀምጦታል።

> የማርክሲዝም መሰረታዊ እሳቤዎች አንዱ "የማምረቻ ኃይሎች" ፣ ምርት እና አገልግሎቶች በሚመረቱበት መንገድ በካፒታሊስት ህብረተሰብ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሀብቶች ጥቅም ላይ በሚውሉበት እና በሚጠቀሙት በማኅበራዊ መደቦች መካከል ግጭት መፍጠሩ የማይቀር ነው ። ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ትግሉ የሚካሄደው በቡርዧው እና በትርፍ ባለቤቶች መካከል ነው። ግጭቱ አንዳንድ ጊዜ እንደ የአስተዳደር ችግር እና የጉልበት ግጭት ፣ አንዳንዴም በቀላሉ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መደቦች መካከል በሚኖር ውዝግብ ይሆናል። እነዚህ ሁለት አካላት በአካል ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብም ወይም በርዓዮተ ዓለም እርስ በርሳቸው የሚታገሉ ናቸው ።

በማርክስ እምነት መሰረት ኅብረተሰብ በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል በሚደረገው ትግል እድገት ያድጋሉ። በማኅበራዊ ለውጥ ውስጥ የሚመጣው በተቃዋሚ መደቦች መካከል ያለው ይህ ትግል ነው። ታሪክ በዚህ የመደብ ትግል ውስጥ ይሻሻላል። የመደብ ትግል የሚመነጨው በታሪክ ውስጥ በአንዱ ክፍል ላይ ሌላኛው ብዝበዛ ሲያካሂድ ነው። በፊውዳሉ ዘመን በፊውዳል ገዥዎችና በገበሬዎች መካከል የነበረ ሲሆን በኢንዱስትሪው ዘመን ትግሉ በካፒታሊስት መደብ (ቡርዧ) እና በኢንዱስትሪው ሰራተኛ(ፕሮሌታሪያት) መካከል ነበር። ክፍሎቹ የጋራ ፍላጎቶች አሏቸው። በካፒታሊዝም ስርዓት ውስጥ ባለራዕዩ ሁልጊዜ ከካፒታሊስት መደብ ጋር

ይጋጫል፡፡ ይህ ግጭት እንደ ማርክስ ገለጻ በመጨረሻ ስርዓቱን በሶሻሊዝም ለመተካት ያስችላል/ያስተካል Marx and Engels (1848)፡፡

የገቢ መጠንና ዓይነት የመደብ ውጫዊ ገጽታ ሲሆን የሚወሰነውም ሰዎች ከምርት መገልገያ መሳሪያ ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው፡፡ በኅብረተሰብ የእድገት ሂደት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የንብረት ይዞታው ዓይነት መለዋዋጥ የመደቦቹን ዓይነት የብዝበዛውን ስልትና በመደቦቹ መካከል የሚደረገውን ትግል ይለውጠዋል፡፡ በዚህም ሂደት ውስጥ የመደቦች ኅልውና መሰረት የሆነው የግል ይዞታ መጥፋት በአንድ ደረጃ ላይ ( በኮሚኒስት ስልተ ምርት) የማይቀር የታሪክ ግዴታ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በማምረቻ መሳሪያዎች በግል መያዝ ምክንያት የመጣው የመደብ ክፍፍል የወል ይዞታው ሲፈጠር ይጠፋል፤ ይህም ማለት በገጠርና በከተማ ፣ በጉልበትና በአዕምሮ ስራ መካከል ያሉት ልዩነቶች ይወገዳሉ ማለት ነው የማርክስም ዋነኛ ዓላማ ይሄ ነው፡፡

## 2.1.6.2 የመደብ ዓይነቶች(type of class)

በዚህ ክፍል የምንመለከተው ማርክስ "socal class" ብሎ የሚጠራውን ነው፡፡ encyclopedia britannica የተሰኘ ድህረ ገጽ መደብ ፣ የመደብ ልዩነት ፣ ማህበራዊ መደብ በአጠቃላይ መደብ በሚል መጠሪያ እንደሚጠቃለሉ ይገልጻል፡፡ መደብ የሚባለውም ተመሳሳይ ማህበራዊና ኢኮኖሚይዊ ደረጃ ያላችው የአንድ ማህበረሰብ ስብስብን እንደሆነም ይገልጻል፡፡ ይህ ጽንሰ ሃሳብ ጥቅም ላይ የሚውለውም ተመሳሳይ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚጋሩ ግለሰቦችን ስብስብ እንዲተካ ተድርጎ ነው፡፡(www.britannica.com/topic/social-class)

በመሆኑም ታይሰን በአሜሪካ የመደብ ስርአት ማህበረሰቦቹ ባላቸው የወል ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ድልድል መሰረት በአምስት ክፍሎች ተከፍለው እንደነበር ትናገራለች፡፡ እነሱም የታችኛው ክፍል (the lower class) ፣ የሰራተኛው ክፍል (the working class) ፣ መካከለኛ ክፍል (the middle class) ፣ የላይኛው/ከፍተኛው ክፍል (the upper class) እና መኳንንቶች(aristocracy) የሚባሉት ናቸው (Tyson, 2006: 55)፡፡ የታችኛው ክፍል

የሚባለው በቤት አልባነት እና በስራ አጥነት የሚኖሩትን ማህበረሰቦች የሚመለከት ነው፡፡ በቂ መኖሪያና ምግብ ፣ ተገቢ ህክምና ፣ በቂ ትምህርት ፣ እና ልብሶች የሌሏቸውን በድህነት የሚሰቃዩትን ማህበረሰቦች የያዘ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ማህበረሰቦች ጊዜያቸውን

በመውለድ ብቻ እያሳለፉ ቁጥራቸውን የሚጨምሩ ፤ መስራት እየቻሉ የማይሰሩ ፤ ሱሰኞች ፤ ወንጀለኞች በመጨረሻም ለበጎ አድራጎት የሚጣሉ እናቶችና አባቶችን የሚያፈራ ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሰራተኛው ክፍል ነው። በዚህ ክፍል የሚመደቡት ሰዎች በትንሹ የተማሩ በጉልበት ስራ የሚተዳደሩ ናቸው። የእቃ አጣቢዎች ፣ ገንዘብ ተቀባዮች ፣ አስተናጋጆች ፣ የቤት ሰራተኞች እና ወዛደሮችን ያጠቃልላል። ለሙያቸው እድገት የላቸውም ለሚሰሩት ስራም ተገቢ ክፍያ አይከፈላቸውም። ብዙውን ጊዜ የሚሰሩ ድሆች ተብለው ይጠራሉ። ሶስተኛው ክፍል መካከለኛ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል አነስተኛ ገቢ ያላቸው እንደ አስተማሪዎች ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ የአነስተኛ ንግድ ባለቤቶች ፣ ጸሃፊዎች ፣ ሃኪሞች ፣ ጠበቆች ፣ የአክሲዮን ደላሎች የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። አራተኛው ክፍል መካከለኛ ከፍተኛ ክፍል ነው።ይህ ክፍል አዲስ ከበርቴ የሚባሉ አይነት ሆነው ከበቂ በላይ ገንዘብ ያላቸው ናቸው። በኢንቨስትመንትና በከፍተኛ የንግድ ስራዎች የተሰማሩትን ያጠቃልላል። የመጨረሻው ክፍል መኳንንት/ከፍተኛ ክፍል የሚባለው ነው። በዚህ ክፍል የሚካተቱ የማህበረሰብ ክፍሎች ባላባቶችና በትውልዳቸው ከከፍተኛ የማኅበረሰብ ክፍል የተገኙ ናቸው። እነዚህ ሰዎች የገቢያቸው ምንጭ በብዛት ውርስ ነው። እጅግ ሃብታም ናቸው። ለእነሱ ገንዘብ ከየትም ይምጣ ግዳቸው አይደለም። ሊያውሉት ከሚችሉት በላይ ገንዘብ አላቸው። ብዙ ጊዜያቸውን በመዝናኛ ቦታዎች ያሳልፋሉ ፤ የሚኖሩበት ሰፈር ከሌሎች ለየት ያለ ነው ፤ ውድ እቃዎች አሏቸው ፤ ልጆቻቸው ምርጥ በሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ይማራሉ ፤ በተለያዩ ማህበራዊም ይሁን ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር ሃይል አላቸው(muhamed aziz, 2017)።

እንደ ማርክስ ግን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ የማኅበረሰብ ክፍሎች ዋናዋናዎቹ ሁለት ናቸው። እነሱም ቡርዧ እና ፕሮሌታሪያትስ ናቸው። ይህንንም ማርክስ በኮሚኒስት ማኒፌስቶ ላይ እንድህ ሲል አስቀምጧል። “Society as a whole is more and more splitting up into two great hostile camps, into two great classes directly facing each other: bourgeoisie and proletariat” Marx & Engels (1848 : 31) በእነዚህ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከመክፈሉ በፊት ግን ሶስት የገቢ ማግኛ መስፈርቶችን አውጥቶ በሶስት ይከፍላቸዋል። የገቢ ማግኛዎቹም 1. ዋና የገቢ ምንጫቸው የጉልበት ሥራ የሆነ ወይም የጉልበት ሰራተኞች 2. ዋና የገቢ ምንጫቸው ትርፍ ወይም ተረፈ እሴት የሆኑ የካፒታሊስቶች ባለቤት እና 3. ዋና የገቢ ምንጫቸው የመሬት ኪራይ የሆኑ ናቸው። በዚህ መሰረት የመደብ አወቃቀር በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም የሰራተኛው ክፍል ፣

ካፒታሊስቶችና የመሬት ባላባቶች ተብሎ ተከፈለ፡፡ በዋናነት ግን ቡርዧ (የመሬት ወይም የካፒታል ባለቤት) እና ፕሮሌታሪያት(የጉልበት ሰራተኛ) ተብለው እንደሚጠሩ Castle (2002 :108) አስቀምጧል፡፡ ሌሎቹ በእነዚህ ውስጥ የሚካተቱ ይሆናሉ፡፡ ግጭቱም በእነዚህ ሁለቱ መካከል ነው፡፡

2.1.6.2.1.1 ቡርዧ

ቡርዧ ወይም የካፒታሊስት መደብ በመባል የሚጠራው የህብረተሰብ ክፍል መሬትና ጥሬ እቃዎችን ጨምሮ ሃብትን የመፍጠርና የማካበት ባለቤትነትን የሚቆጣጠሩ ከቁጥር አንጻር ሲታዩ እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎችን ያቀፈ ነው፡፡ ማዕድናትን በማስወጣት ፣ ፋብሪካዎችን በመፈብረክ እና የተለያዩ ዘመናዊ ቴክሎጅዎችን ሰራተኞችን ቀጥረው በማሰራት በርካታ ገንዘብ ያካብታሉ፡፡ እነዚህ "ያላቸው" ተብለው የሚጠሩ ሲሆኑ ተፈጥሮን ፣ ኢኮኖሚነና የሰው ኃይልን ይቆጣጠራሉ፡፡ለስራ የሚገለገሉባቸውንም የሰው ኃይሎች አነስተኛ ዋጋ በመክፈል የጉልበት ብዝበዛ ያካሂዳሉ(Tyson,2006:71)፡፡

2.1.6.2.1.2 ወዝ አደር (proletariat)

ፕሮሌታሪያት የሚለውን ቃል encyclopedia እንድህ ሲል ይተረጉመዋል፡፡

> ፕሮሌታሪያት የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል የተገኘው ፕሮሌታሪየስ ከሚል የላቲን ቃል ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ከክርስቶስ ልደት በፊት በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ቃሉ አገልግሎት ላይ የዋለው ንብረት የሌላቸውን የሚያካትት የህዝብ ቆጠራ ምድብ ለመመደብ ነበር፡፡ ይህ ቃል ወደሌሎች ቋንቋዎችም ሲመጣ ይህንኑ ትርጉም ይዞ ነው፡፡ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሆነውንና ዝቅተኛውን መደብ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ትኩረትና የተለየ ትርጉም እያገኘ መጣ፡፡ የተጎዱትንና በካፒታሊስቱ ማህበረሰብ የተጨቆኑትን የህብረተሰብ ክፍል አመልካች ቃል ሆነ፡፡ (www.encyclopedia.com)

እነዚህ ማህበረሰቦች በካፒታሉ ወይም ቡርዧው ስርዓት ውስጥ ያለውን ስራ ሁሉ የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ ለሚያፈሩት ሃብትና ንብረት ግን ቁጥጥር የላቸውም ወይም ተጠቃሚ አይደሉም፡፡ ብዙውን ጊዜ በእጅ ስራ ሙያ የሚሰማሩ ናቸው፡፡ ማእድን ማውጣት ፣ የፋብሪካ ስራ ፣ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር ፣ የባቡር ሃድድ እና የመሳሰሉትን በመስራት የሀብታሞችን ካዝና የሚሞሉ ናቸው(Tyson,2006:71)፡፡ ስለዚህ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ከካፒታሉ ጋር ያላቸው ግንኙነትም የበዝባዥና የተበዝባዥ ነው፡፡

### 2.1.7 ስርአተ ጾታ (gender )

በዚህ ክፍል ሥርዓተ ጾታ ሲባል የእንግሊዝኛውን Gender ለማለት ነው። ሥርዓተ ጾታ፣ ከሥነህይወታዊ ደንብ ውጭ በሆነ መልኩ በማኅበራዊ ምደባ (Social stratification) ምክንያት የምናገኘው ወንድነት ወይም ሴትነት ነው። ይህንኑ ሃሳብ Reeves እና Baden (2000፡30) ሥርዓተ ጾታ ማለት የሰው ልጅ ሥነህይወታዊ ባህሪ በባህል ዋጋ ተሰጥቶትና ተፈክሮ በማኅበረሰቡ ለሴትነት ወይም ለወንድነት የሚያበቃ መስፈርት የሚበጅበት ሥርዓት ነው ሲሉ ይገልጹታል። Holmberg (2005:8) ከላይ የተባለውን ፍቺ በሚያጠናክር መልኩ ሥነህይወታዊ ጾታ (Biological sex) ማኅበራዊና ባህላዊ በሆነ መንገድ እንደገና መልክ የሚሰጥበት ነው ሲሉ አብራርተውታል። ሌሎች (Olasupo and et als. 2012:11) ደግሞ ይህንኑ ቃል ማኅበራዊ በሆነ መልኩ የተቀናጁ ሚናዎች ተለይተው ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጡበት ስልት ነው በማለት ያስረዳሉ። Kiriti (2011፡13)ም ማኅበረሰቡ ለሴትና ለወንድ ለይቶ የሰጠው ሚና ነው፤ በመሆኑም ሥርዓተ ጾታ የሴቶችና የወንዶች ማኅበራዊ ማንነት (social identity) ነው ሲሉ ገልጸውታል። በዚህ ሂደት ውስጥ ማኅበረሰቡ ጾታን መሰረት ያደረገ ደንብና ማኅበራዊ ሚና አበጅቶና ሰጥቶ እናገኛለን። እንዲህ ዓይነቱ ምደባ ከጾታ ጋር ምንም የሚያገናኘው ጉዳይ ካለመኖሩም በላይ ምደባው የግለሰብ ምርጫ አይደለም። ይሄ (ሥርዓተ ጾታዊ ምደባ) ባህላዊ አስተሳሰብ ስለመሆኑ Palmisano (2001:267) ሥርዓተ ጾታዊ ማንነት ሙሉ በሙሉ ግለሰባዊ ምርጫ አይደለም፤ የባህል ጫና ባረፈባቸው በሥርዓተ ጾታዊ ሚናዎች፣ በደንቦች እና በማኅበራዊነት ላይ የተመሰረተ ነው። ራሳችንን ወንድ ወይም ሴት ብለን ለመወሰን ያደግንበት ባህላዊ አስተሳሰብ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ባህል የየራሱ የሆነ የሥርዓተ ጾታ አስተሳሰብ አለው ሲሉ ገልጸውታል። ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ፆታ በማኅበራዊና ባህላዊ ክንውን ውስጥ ያለ ጽንሰ ሃሳብ ነው ማለት ነው (Nenola 1993፡50 in Fekade 2003)። Kabeer (1996:17) የቃሉን ፍችና ሚና ከፍ አድርገው፣ ተቋሞች የተደራጁበትና እንደገና የተዋቀሩበት መንገድና ውጤት እንዲሁም ግንኙነቱ በነዚህ ተቋማት ውስጥ የሰረጸ ሥርዓት መሆኑን አጠንክረው ገልጸውታል። አንዳንዶቹ ሥርዓተ ጾታን “The systematic domination of females by males” በማለትም በይነውታል (Palmisano 2001:266)። ባጠቃላይ ሥርዓተ ጾታ ባህላዊና ማኅበራዊ በሆነ አስተሳሰብ ተፈጥሯዊ ጾታን መነሻ አድርጎ ለሴቶችና ለወንዶች ተለይቶ ሚና የተሰጠበት፣ ይሄም ሚና ለበላይነትና ለበታችነት ምክንያት የሆነ ደንብ ነው

ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ሥርዓተ ጾታ ሲባል ይህንን የተመለከተውን ማለት ነው፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ

በዚህ ንኡስ ርዕስ ስር ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደም የተሰሩ የምርምር ስራዎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ እንደ ንድፈ ሃሳቡ ጥልቀት እና እንደ አማርኛ ረጅም ልቦለዶች የጭብጥ ሁኔታ በውስጥ ቋንቋ (በአማርኛ) በተጻፉ ልቦለዶች ላይ ይህን ያህል ተሰርቷል ማለት ባይቻልም በውጭ ቋንቋ (በእንግሊዝኛ) በተጻፉ ልቦለዶች ላይ እና በውጭ ደራሲዎች ላይ በውጭ ቋንቋ (በእንግሊዝኛ ቋንቋ)የተሰሩ ጥናቶችና ከዚህ ጥናት ርዕስ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተወሰኑ ጥናቶች ከሞላ ጎደል በዚህ ክፍል ተዳሰዋል፡፡ እነዚህም እንደተሰሩበት የጊዜ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

በንድፈ ሃሳብ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች አንደኛ በአብይ ዳንኤል አምባቸው (SOCIALIST REALISM AND ITS IMPLICATIONS FOR THE AFRICAN WRITER ፣ 1986) በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናት የሶሻሊስት እውነታዊነት (socialist rialism) በተመረጡ የአፍሪካ ጸሃፍት ያለውን አንድምታ የተፈተሸበት ነው፡፡ በዚህ ጥናት የደቡብ አፍሪካ ፣ የሰሜን አፍሪካ ፣ የምዕራብ አፍሪካና የመካከለኛው አፍሪካ የሥነ ጽሁፍ ስራዎችና ጭብጦቻቸው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሶሻሊስት እውነታዊነት በአፍሪካ ጸሃፍት ያለውን አንድምታ መፈተሽ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚጋራው ጉዳይ በማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ላይ መመስረቱ ነው፡፡ የሚያላያያቸው ጉዳይ አብይ ከማርክሲዝም ጭብጦች ውስጥ የሶሻሊስት እውነታዊነትን ብቻ ሲዳስስ የእኔ ጥናት ከዚህ ውጭ የሆኑ ጭብጦችን መዳሰሱ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአብይ ጥናት የጸሃፍቱን አንድምታ የሚፈትሽ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ ንድፈ ሃሳቡ በልቦለዱ ላይ እንዴት እንደተንጸባረቀ የሚፈትሽ መሆኑ ይለያቸዋል፡፡

ሁለተኛ በምስራቅ ታረቀኝ (ALIENATION IN THREE AMHARIC NOVELS: Fɨk'ɨr ɨskä Mäk'abɨr, Adäfrɨs and Kadmas Bašagär ፣ 2002) የሚል ርዕስ ነው፡፡ ይህ ጥናት ሶስት በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ልቦለዶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ልቦለዶቹም የሃዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" ፣ የዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስ" እና የበአሉ ግርማ "ከአድማስ ባሻገር" የተሰኙ ናቸው፡፡ ጥናቱ በሶስቱ ልቦለዶች ላይ ባይተዋርነት እንዴት እንደተቀመጠ ያሳያል፡፡ ዋና

ዓላማውም ባይተዋርነት በልቦለዶቹ ላይ እንዴት እንደተንጸባረቀ ከማርክስ ንድፈ ሃሳብ አንጻር መተንተን ነው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ከንድፈ ሃሳብ በተጨማሪ በአማርኛ ልቦለዶች ላይ የተሰራ በመሆኑ ቅርርቦሽ አለው፡፡ የሚለያቸው ነጥብ የምስራቅ ጥናት ከማርክሲዝም ጭብጦች በባይተዋርነት ላይ ብቻ የተገደበ ሲሆን የኔ ከባይተዋርነት ውጭ የሆኑ ጭብጦች ማለትም ርዕዮተ ዓለም ፣ ቁሳዊነትና መደብ ላይ የሚያተኩር መሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለትንተና የተጠቀምናቸው ልቦለዶች የተጻፉበት ዘመን የተለያየ ነው፡፡

ሶስተኛ በሚካኤል ፍ/ማርያም (A STUDY OF THE INFLUENCE OF MARXISM ON BEALU GIRMA'S THREE NOVELS: HADDIS, YEKEY KOKEB TIRI, AND DERASIW ፣ 2008) በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ስራ በበአሉ ግርማ ሶስት ልቦለዶች ላይ ማለትም ሃዲስ ፣ የቀይ ኮከብ ጥሪና ደራሲው ላይ የተደረገ ነው፡፡ በጥናቱ ላይ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ በበአሉ ድርሰቶች ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ እና ጸሃፊው የሚያንጸባርቀው ርዓዮተ አለም ተዳሰውበታል፡፡ ዋና ዓላማውም የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ በበአሉ ድርሰቶች ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳሳደረ መፈተሽ እና በአሉ በልቦለዶቹ ላይ የሚያንጸባርቀውን ርዕዮተ ዓለም ማሳየት ነው፡፡ ይህም ጥናት ከሌሎቹ በተመሳሳይ በማርክስ ፍልስፍና ላይ የሚያጠነጥን መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የሚለያያቸው ደግሞ ሚካኤል በልቦለዶቹ ላይ የንድፈ ሃሳቡ ተጽዕኖ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ ንድፈ ሃሳቡ በልቦለዶቹ ላይ እንዴት እንደተንጸባረቀ ማሳየት መሆኑ ነው፡፡ ለትንተና የተመረጡት ልቦለዶችም እንዲሁ የተጻፉበት ዘመን የተለያዩ ናቸው፡፡

አራተኛ በባለው ደምሴ (Ideology and the Representation of Female Characters in Ngugi wa Thiong'o's The River Between and A Grain of Wheat ፣ 2009) በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናት "The River Between" እና "A Grain of Wheat" በተሰኙ ሁለት የ Ngugi ልቦለዶች ውስጥ ርዕዮተ ዓለምና የሴቶች ገጸ ባህሪ ውክልና ተዳሶበታል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በ Ngugi ልቦለዶች ላይ የሴቶች ገጸ ባህሪን ውክልና እና የርዕዮተ ዓለምን ውጤት መመርመር ነው፡፡ ይህ ጥናት ርዕዮተ ዓለም ላይ በማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የሚያለያያቸው ደግሞ የባለው ጥናት የሴት ገጸ ባህሪያት ውክልና እና ርዕዮተ ዓለምን ብቻ ነጥሎ የሚያይ ሲሆን የእኔ ጥናት ርዕዮተ ዓለምን በአጠቃላይ ይዳስሳል፡፡ ከልቦለዶቹ አንጻርም የባለው ጥናት በውጭ ቋንቋ በተጻፉ ልቦለዶች ላይ ሲያተኩር የእኔ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ በተጻፉ ልቦለዶች ላይ መሆኑ ልዩነት እንድኖር አድርጓቸዋል፡፡

አምስተኛ በፍስሃ ተስፉ (Ideology in selected east African Anglophone noveles : a comparative study of post-colonial experience ፣ 2009) በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናት ለሶስተኛ ድግሪ ማሟያነት የተሰራ ሲሆን ርዕዮተ ዓለም በእንግሊዝ ቅኝ በተገዙ ምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ልቦለዶች ላይ በቅኝ ግዛት በኋላ ያለውን ሁኔታ በንጽጽር መልኩ የቀረበበት ነው፡፡ ከምስራቅ አፍሪካ ሃገሮችም በኬኒያ ፣ ኡጋንዳና ሱማሊያ የተጻፉ ልቦለዶች ላይ ያተኩራል፡፡ ዋና ዓላማውም የርዕዮተ ዓለምን አወቃቀር በመመርመር የርዕዮተ ዓለምን ምንነት ለማብራራት እና ርዕዮተ ዓለም ከማኅበረ ፖለቲካዊ ውክልና ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመርመር ያለመ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ድህረ ቅኝ ግዛትንም ይዳስሳል፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚጋራው ነጥብ አለ፡፡ ይኸውም ርዕዮተ ዓለምን መዳሰሱ ነው፡፡ የሚለያያቸው ጉዳይ ደግሞ የፍስሃ ጥናት ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ቅኝ በተገዙ የምስራቅ አፍሪካ ሃገሮች በተጻፉ ልቦለዶች ላይ ሲያተኩር የእኔ ጥናት ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አንዱ በሆነው በ "አማርኛ" ቋንቋ በተጻፉ ልቦለዶች ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ ከዓላማም አንጻር ቢሆን የእኔ ጥናት የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ እንዴት በልቦለዶቹ ላይ እንደተንጸባረቀ ማሳየት በመሆኑ እና ከድህረ ቅኝ ግዛት አንጻር ባለመዳሰሱ ይለያል፡፡

ስድስተኛ በትኋደድ እድሜ (ሙስና በያልታበሱ እንባዎች እና በአፈላማ ልቦለዶች ውስጥ ፣ 2011 ዓ.ም) የሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናት በውስጥ ቋንቋ(በአማርኛ ቋንቋ) የተሰራ ሲሆን ሙስናም በማርክሲዝም ስር ከሚነሱ ጭብጦች አንዱ በመሆኑ በሁለት ልቦለዶች ላይ ማርክሳዊ ንባብ አካሂዳለች፡፡ ይህም ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡ የሚለየው ደግሞ ትኋደድ ትኩረቷን ሙስና ላይ ብቻ ስታደርግ እኔ ሌሎች የማርክሲዝም ጭብጦች ላይ መሆኑ እና ትኩረት ያደረኝባቸው ልቦለዶች የተለያዩ መሆናቸው ነው፡፡

በልቦለዶቹ ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎችን በሚዳሰሱበት ወቅት ከሶስቱ ልቦለዶች በአንዱ ላይ ተሰርቶበታል፡፡ ይህ ልቦለድ *በፍቅር ስም* ሲሆን የተሰራበት ርእስ "የእኔነት ሃተታ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ለቦለዶች " በሚል በሰብለ ወልደኪዳን (2010) የተሰራ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በፍቅር ስምን ጨምሮ ሌሎች ሶስት የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ተዳሰውበታል፡፡ ይህ ጥናት ከስነ ልቡና ንድፈ ሃሳብ አንጻር የተሰራ በመሆኑ መጽሃፉን በእኔ ጥናት ከማርክስ ንድፈ ሃሳብ አንጻር እንዳየው አድርጎኛል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# ትንተና

## 3.1 የልቦለዶቹ አጽመ ታሪክ

### የአፐቢያ (1999 ዓ.ም) ረጅም ልቦለድ አጽመ ታሪክ

አፐቢያ ረጅም ልቦለድ መቼቱን አዲስ አበባ አራት ኪሎ ያደረገ ነው። አምስት ዋና ዋና ገጸ ባህሪያት አሉት። እነሱም ታፈሰ ፣ ዶክተር ማርቆስ ፣ ሙሉጌታ ፣ እርጥባንና ኮምሬድ ናቸው። ታፈሰ የእርጥባን አባት ሲሆን ሃብታም ተደርጎ የተሳለ ገጸ ባህሪ ነው። የተወለደው አራት ኪሎ ውስጥ ከምትኖር ሴተኛ አዳሪ ነው። አባቱ ሃብታም በመሆኑ ከሴተኛ አዳሪ እናቱ ነጥቆ ከእርሱ ጋር ያሳድገዋል። መጨረሻም የአባቱን ሀብት በመውረሱ ሀብታም ይሆናል። ሀብታም ከሆነ በኋላ አራት ኪሎ የሚኖሩ ድሆችን አስነስቶ ቦታውን በ"ኢንቨስትመንት" ለማልማት በኅበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ የሚገኝ ሰው ነው።

ዶክተር ማርቆስ ደግሞ የሶሽዮሎጅ (ማኅበረሰብ ጥናት) ትምህርት ክፍል ያጠና እና በአንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በመምህርነት ሙያ ተሰማርቶ የሚያገለግል ሰው ነው። ዶክተር ማርቆስ ከታፈሰ ጋር ታቃራኒ አስተሳሰብ ያለው ነው። ታፈሰ ለደሃ(ዝቅተኛ የማኅበረሰብ) ክፍሎች ንቀት ያለው እና እነሱንም ለመጨቆን የሚታትር ነው። ልጁ እርጥባን ደግሞ የዶክተር ማርቆስ ተማሪ ናት። እርጥባን የመመረቂያ ጽሁፏን ልትሰራ የተዘጋጀችው በ "ልመና" ላይ ነበር። ነገር ግን ዶክተር ማርቆስ አራት ኪሎ በሚገኙ ተፈናቃዮች ላይ ጥናቷን እንድታደርግ በመፈለጉ በሱ ሀሳብ ተስማምታ የጥናቷን ትኩረት አራት ኪሎ በሚገኙ ማኅበረሰቦች ላይ ታደርጋለች። ይህንን ግን አባቷ እንድታደርግ አይፈቅድላትም፤ ቢሆንም እሷ ትቀጥላለች።

ሙሉጌታ እና ኮምሬድ የተባሉት ገጸ ባህሪያት ደግሞ አራት ኪሎ ካፈራቻቸው እና የገፈጡ ቀማሽ (ተፈናቃይ) ከሆኑት ማኅበረሰቦች መካከል ናቸው። ሙሉጌታ ምንም እንኳ ከአካባቢው ራቅ ብሎ በሚገኝ ቦታ በመምህርነት ሙያ ተሰማርቶ ይሰራ የነበረ ቢሆንም ከአካአቢው ተለይቶ መኖር ባለመቻሉ እና ሴት አያቱ ከሱ ውጭ ረዳት የሌላቸው በመሆኑ ከጎናቸው ለመሆን በማሰብ ስራውን ለቆ በስራ ፈትነት በአራት ኪሎ የሚኖር ነው። ምንም እንኳ የአራት ኪሎን መፍረስ እና የማኅበረሰቦቹን መበተን አጥብቆ የሚቃወም ቢሆንም ይህን ጉዳይ

የማስቆም አቅም የሌለው በመሆኑ የሚሆነውን ቁጭ ብሎ የሚጠብቅ ሆኗል። በመጨረሻም እርጥባን ጥናቷን ለማካሄድ ስትነሳ መረጃ የሚሰጣት ሰው ስታፈላልግ ከሙሉጌታ ጋር ትገናኛለች። ሙሉጌታም ስለ አካባቢው ሰዎች የአኗኗር ይትባህል ፣ ጸባይ ፣ የገቢ ምንጭ ፣ የልጆች አስተዳደግ ፣ አካባቢውን ለቀው ቢሰደዱ ስለሚደርስባቸው የኑሮ ቀውስ ፣ በአራት ኪሎ ስለሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች አኗኗርና አሟሟት ሳይቀር ይነግራታል። በዚህ መካከል ታፈሰ ሙሉጌታን ከእሷ እንዲርቅና መረጃዎቹንም እንዳይሰጣት ያስጠነቅቀዋል። ሙሉጌታ ግን ምንም ቢለው ሊሰማው አልቻለም። ታፈሰም ያስደበድበዋል። በዚህ መካከል እርጥባን አፍ አውጥታ ልትነግረው ያልቻለችው ፍቅር ጭምር ከውስጧ ስለነበር ቤቷን ለቃ ከሙሉጌታ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ መኖር ትጀምራለች።

በመጨረሻም አባቷ(ታፈሰ) አራት ኪሎ ከምትገኝ ሴተኛ አዳሪ እንደተወለደ የሚያረጋግጥ ፤ ታፈሰ ከሴት አዳሪ እናቱ ጋር ሆኖ የሚያሳይ ምስል(photo) ከነታፈሰ ቤት አምጥቶ ለእርትባን እና ለታፈሰ ይሰጣቸዋል። ይህች ሴት በችግር ተሰቃይታ እንደሞተች ታሪኳን ለእርጥባን ከነገራት ሴቶች መካከል አንዷ ነበረች።

## *የበፍቅር ስም* (2009 ዓ.ም) ረጅም ልቦለድ አጽመ ታሪክ

የዚህ ልቦለድ ታሪክ የሚያጥነጥነው በዋናነት ሰባት ሴት ልጆቹና አንድ ወንድ ልጅ ስላሉበት ቤተሰብ ነው። ሴት ልጆችን አብዝተው በመውለዳቸው አባትየው(ብዜን) ሲከፋ ይስተዋላል። የለቦለዱ ዋና ገጸባህሪ ወንዱ ልጅ ሲሆን ስሙ ታለሰው/አላዛር ይባላል። በታሪኩ ሂደት የሚታየው ታለ በብዙ ሴቶች መካከል በማደጉ የ"ሴትነት" ባህሪ የተላበሰ ሆኖ ነው። ከሰባቱ ሴቶች መካከል የሱ ታላቅ የሆነችው ቻየና ከታለ በተቃራኒው የ"ወንድነት" ገጽታ ተላብሳ ትታያለች። ታለን "ሴታሴት" በመሆኑ ሲንቁት ቻይናን ግን "ወንዳወንድ" በመሆኗ ያሞግሷታል።

ታለሰው/አላዛር በሽተኛ የነበረ ቢሆንም (በእሱና በቤተሰቡ እምነት) በኦፉ አቡኮ ድግምት አማካኝነት በሽታውን የጎረቤት ልጅ ለሆነው ለቹቹ አዘዋውረውለታል። በዚህም ምክንያት የጥፋተኝነት ስሜት ስለሚሰማው ከቤት አይወጣም ነበር። በዚህ ሁኔታ እያለ ሲፈን የተባለች ልጅ በፍቅር ወደ ህይወቱ ትመጣለች። ቢሆንም ግን በሚያሳያችው የ"ሴትነት" ጸባይ ትንቀዋለች።ከዚህ በኋላ ግን የሱ ታላቅ(ቻይና) ከቤት ይዛው በመውጣት ከወንድ ጓደኞቿ ጋር ታስተዋውቀውና "ውንድነት" ታለማምደዋለች። እሱም ተግቶ ይለማመዳል። ምንም እንኳ

"ወንድ"ነቱን በልምምድ ቢያገኘውና ከሲፊን ጋር የፍቅር ግንኙነት ቢጀምሩም የሱ በሽታ በድግምት ወደ ቹቹ በመገልበጡ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማው ያደርገዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ከሲፊንጋም ይለያያሉ፡፡

### *የታለ በእውነት ስም* (2011 ዓ.ም) *ረጅም ልቦለድ አጽመ ታሪክ*

*ታለ በእውነት ስም* ረጅም ልቦለድ የበፍቅር ስም ረጅም ልቦለድ ተከታይ ነው፡፡ ታሪኩ በመጀመሪያው የሚቀጥል ነው፡፡ ገፀ ባህሪያቱም ራሳቸው ሆነው የተወሰነ የህይወት ለውጥ ያደረጉ ናቸው፡፡ ታለ ትምህርቱን ከአቋረጠበት ቀጥሎ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የፍልስፍና ትምህርት ይማራል፡፡ የእህቱ ባል(የስምረት) ከሆነው ጠና ጋሻው/ሻምበል ጋር ጥሩ ጓደኝነት ይመሰርታሉ፡፡

ከነቹቹ ቤት በቤተ ክህነት ሙያ የሚያገለግሉ አባትና ልጅ ተከራይተው ይገባሉ፡፡ የልጁ ስም ረድ ሰርዌ ይባላል፡፡ ረድ ሰርዌ ሃይማኖታዊ ስልጣኑን ምክንያት በማድረግ ከታለሰው እናት(አንጓች) ጥቅማ-ጥቅም ያገኝ ነበር፡፡ ለሚያገኘው ጥቅማ-ጥቅም ምላሽ ጸበል፣ እምነት እና ጸሎት የመሳሰሉትን በበኩሉ ያበረክታል፡፡ በዚህ ሁኔታ አባቱን ይዞ ይኖራል፡፡ በኋላ የቤተ ክህነቱን ትምህርት በመተው አሰኳላ ትምሮ ዩኒቨርሲቲ ይገባል፡፡ ከታለ ጋ በድጋሜ ይገናኛሉ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ደግሞ በደጋሜ ጫት ቤት የገናኛሉ፡፡ ከዛም አባቴ ሰዎች ጋር እንዳልስማማ አስደግመውብኛል የሚለ እምነት እንደያዘ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ የሆነችው የታለ እህት/አበባ ጸልያለት ጸሎቱንም "አሜን" ብሎ ተቀብሎ ታሪኩ ያልቃል፡፡

## 3.2 ርዕዮተ ዓለም በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ

ርዕዮተ ዓለም የግለሰቦችን ምናባዊ ሃሳቦችና እውነተኛው የኑሮ ሁኔታ ያላቸውን ዝምድና እና ውክልና ይመለከታል(Althusser, 1971: 181)፡፡ ለምሳሌ ሃይማኖታዊ ፣ ስነ-ምግባራዊ ፣ ህጋዊ ፣ፖለቲካዊና ሌሎች አስተሳሰቦችን መጥራት ይቻላል፡፡ ሌሎችንም የዓለም አመለካከቶች ብንመለከት በእኛ ልማድ እያንዳንዱን ርዕዮተ ዓለም እውነተኛ ናቸው ብለን አምነን የተቀበልናቸው ናቸው፡፡ በአመዛኙ ግን ምናባዊ ናቸው ከእውነታው ጋር አይዛመዱም (Althusser,1971: 182)፡፡ በመሆኑም በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ምን አይነት ርዕዮተ አለም የምንን እውነተኛነትና ምናባዊነት እንደሚጠቁሙ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ ምን አይነት ርዕዮተ ዓለም እንደተነጸበረቀ ትንታኔ ለመስጠት ትኩረት የተደረገው በመጽሃፉ ውስጥ ብቻ ያለውን ትረካ መሰረት ያደረገ ሲሆን የገጸባህሪያቱን የኑሮ ሁኔታና ምልልስም ትኩረት ተደርጎባቸዋል፡፡

በመሆኑም በልቦለዱ ውስጥ የተንጸባረቀውን ርዕዮተ ዓለም ከማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ አንጻር ምን እንደሚመስል ማሳየት የጥናቱ ዋነኛ ሥራ ነው።

### 3.2.1 ሃይማኖት በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች

ሃይማኖትን በተመለከተ በ*አጥቢያ* ረጅም ልቦለድ ውስጥ ኮምሬድ የተባለው ገጸባህሪ የሚያንጸባርቀው ርዕዮተ ዓለም አለ። እንደሚታወቀው በክርስትና እምነት እየሱስ የመጣው ከእግዚአብሄር ተልኮ የሰው ልጆችን ለማዳን ነው። ትረካው የሚያስረዳን ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ነው። ይኸውም እየሱስ ከእግዚአብሄር የተላከ ሳይሆን ከአንድ ዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍል በመጥምቁ ዮሃንስ አማካኝነት የተመለመለ እና ድሆችን ከጭቆና ለማውጥት ዓላማ የሚታገል ጀግና ተደርጎ ተገልጿል።

> ...መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን መለመለው። እየሱስም ለአርባ ቀን ወደ ምድረ በዳ በመዝለቅ በአሲኖች ደንብ አበለጸገ። አስተምህሮቱም ከአሲኖች የተገኘ ነው። **<u>ገንዘብ የሀጢያት ሁሉ ስር ነው</u>** ይለናል። ከዚህ በፊትም ሆነ በኋላም ሀብትን በዚህ መንገድ የገለጹ እነሱ ብቻ ነበሩ። “ሀብታም መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ መሹለክ ይቀለዋል” ይላል። ብዙሃኑ እስራኤላዊ በድህነት ስር ስለነበር ነው። የተከማቸ ሃብታችሁን አከፋፍሉ የሚል አቋም የያዘው በእነሱ ነው።
>
> **<u>“የእየሱስ ዓላማ የድሆች ተስፋ መሆን ነው።</u>** ተጨቋኞችን በጨቋኞች ላይ ማስነሳት ነበር እንጅ ከንቱ የእግዚአብሄርን መንግስት መስበክ አልነበረም። **<u>ጥምቀትን የተጠቀመበት ሥነ ልቦናቸው ለራሳቸው ካላቸው ግምት ጋር የወደቀውን ድሆችን የእግዚአብሄር ልጅ በማድረግ በሞራል እንድያንሰራሩ ለማድረግ ነው።</u>** [...] በወቅቱ “አባት” ይባሉ የነበሩ የቤተ መቅደስ ሹማምንቶችንና የመሬት ግብር ሰብሳቢዎች ከተከበሩበት የድሆች ልብ ውስጥ በአንዲት ቃል አስወጥቶ ጥሏቸዋል። “ከሰማይ አባታችሁ ውጪ ማንንም አባት አትበሉ!” ብሎ በማስተማር(አጥቢያ፤1999፣127 - _128)።(አጽንኦት ተጨምሯል)

Tyson (2006 : 59) እንዳስቀመጠችው ማርክስ “ሃይማኖት ሰዎችን እንዲያንቀላፉ የሚያደርግ አደንዛዥ እጽ ነው (Religion is the opiate of the masses)” ሲል ይናገራል ትላለች። የሃይማኖት ርዕዮተ ዓለም ድሆች በህይወታቸው ውስጥ ረክተው እንዲኖሩ ወይም ታጋሽ እንድሆኑ ያደርጋቸዋል ይላል። በዚህም አብዛኛው የህብረተሰቡ ክፍል ብዝበዛ ላይ የወደቀ ነው የሚል የማርክሲስቶች አመለካከት እንዳለ ትገልጻለች። በልቦለዱ ውስጥ ኮምሬድ እንደሚለው እየሱስ የመጣውም ለዚሁ ዓላማ እንደሆነ ነው። ይህም እየሱስ እና ተከታዮቹ በሃይማኖት ሰበብ የሰዎችን ሥነልቡና ለማጠናከር እንደተጠቀሙበት ያሳያል። እየሱስም መሪ

ሆኖ የመጣው የእግዚአብሔርን መንግስት ለመስበክ አይደለም። ይልቁንስ ድሆች በሰማይ አባት አለን በሚል ተስፋ ተጽናንተው እንድኖሩ ለማድረግ የገዢው መደብ የተጠቀመበት ስልት ነው። ለዚህም ሥነልቡናቸውን ለማጽናት ይረዳው ዘንድ ጥምቀት ይሰጣቸዋል።

Tyson (2006: 59)እንዳስቀመጠችው የማርክሲስቶች ሃይማኖት ላይ ያለቸው ጥያቄ የእግዚአብሔር መኖር አለመኖር አይደለም። የእነሱ ትልቁ ትኩረት ሰዎች በተደራጀ ሃይማኖት ስም ምን ይሰራሉ? የሚል ነው። Althusser (2014 : 195) እንደምሳሌነት የክርስትና ሃይማኖትን በመውሰድ ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የሚሰሩ ስራዎች ያብራራል። የክርስትና ሃይማኖት በአለም ላይ ያሉ ድሆችን በማልበስ ፣ በመመገብ መጠለያ በመስጠት አልፎ ተርፎም እስከማስተማር ድረስ ይረዳሉ። ከዚህ እርዳታ ጋር ተያይዞ “ድሆች አመጸኛ ካልሆኑ ዋጋቸውን በሰማይ ያገኛሉ” የሚል አስተምህሮ ይሰራጫል(Tyson, 2006 : 59)። በዚህም ድሆች በሃብታሞች ላይ  እንዳያምጹ እገዳ ያደርግባቸዋል። እንዳያምጹ ከማድረጉም ባሻገር “ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል” (ማቴ ፤ 19፣24) የሚል የመጽሃፍ ቅዱስን ቃል በመጥቀስ ሀብትን የሃጢያት ሁሉ ምንጭ አድርጎ የመቁጠር አስተምህሮ በማስፋፋት ድሆች በካፒታሊስቶች እንዲበዘበዙ ያደርጋቸዋል የሚለው የማርክሲዝም እይታ ነው። በዚህ ልቦለድም ውስጥ ኮምሬድ የተባለው ገጸ ባህሪ “እምነት የመጨቆኛ መሳሪያ ነው”(አጥቢያ ገጽ 125) ሲል የማርክሲስቶችን አስተምህሮ ይደግመዋል። ኮምሬድ እንደሚለው የክርስትና ሃይማኖት የተጠነሰሰው ከክርስቶስ ልደት በፊት “ኢሴንስ” በተባሉ እስራኤላውያን እንደነበር ነው። እነዚህ እስራኤላውያንም በሃይማኖት መሪዎች ብዝበዛ እና ጭቆና ይደረግባቸው ነበር። ባርነትንም አጥብቀው ከመቃወማቸው ባሻገር ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንድኖር ይሹ ነበር። የእየሱስ መሪ መጥምቁ ዮሃንስም ከእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ወጥቶ እየሱስን ለመሪነት እንደመለመለው ይናገራል(አጥቢያ ገጽ 127)።

Tyson (2006:56) በማርክሲዝም አመለካከት “ሃይማኖት የመጨቆኛ መሳሪያ ነው” መባሉም እምነትን መቃወም አይደለም። ይልቁንም እምነቱን መታገጊያ በማድረግ “ካፒታሊስቶች” ድሆችን ከአመጽ የተቆጠቡ በማድረግ ሃብትና ስልጣናቸውን ጠብቀው ለማቆየት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው ብለው ያመናሉ ትላለች። በልቦለዱም ውስጥ ኮምሬድ ይህንኑ ሲናገር ይሰማል።ኢኮኖሚያዊ መደባቸው ከፍተኛ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ድሆችን/ዝቅተኛውን የህብረተሰብ ክፍል ለመበዝበዝ ሃይማኖትን እንደመጠቀሚያ ያደርጉታል ይላል። ቤተክርስቲያን የከሸፈች የአብዮት ተቋም ስትሆን ክርስቲያኖችም አመጻቸው የተቀለበሰባቸው

የመጀመሪያዎቹ ሶሽያሊስቶች ናቸው(አጥቢያ ገጽ 126)ይላል፡፡ በመሆኑም ማርክሲስቶች እንደሚሉት ሃይማኖትን ሰበብ በማድረግ የሚጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ እየሱስም በጭቆና ውስጥ የሚኖሩትን ዝቅተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች ተስፋ ሊሆናቸው እንደመጣ ይናገራል(አጥቢያ ገጽ 127)፡፡

በሌላ በኩል *በታለ በዕዉነት ስም ረጅም* ልቦለድ ውስጥ ረድ ሰርዌ የተባለው ገጸ-ባህሪ አንጓችን (የታለን እናት) ሃይማኖትን ተገን በማደረግ ሲጠቅምባት ይስተዋላል፡፡ በዚህም ምክንያት ታለ ይቃወመዋል፡፡ ረድ ሰርዌ ፀሎት(ይሁንም አይሁንም) ቆሞ በሚያነበንብበት ጊዜ የታለ እናት ነጠላዋን አጣፍታ ስትከታተለው ይታያል፡፡ ለዚህ ለሚያነበንበው ፀሎት መሳይ ነገር ድጎማ ይደረግለታል፡፡ ከምግብ ምግብ ተመርጦ ለቁስ አባቱ ይሰጣል፡፡ይህ ድጎማ የሚደረግለት "ሰው" በመሆኑ አይደለም ይልቁንስ የቤተ ክህነት ባለሙያ በመሆኑ ከሚያደርገው ፀሎት ፣ ቅዱሳን መጻህፍትን ደግሞ ከሚረጨው ፀበል ፣ በየገዳማቱ በሚጎበኝበት ወቅት ከሚያመጣው እምነት በመቋደስ የበረከት ተካፋይ ለመሆን እንጅ፡፡ ነገር ግን በሃይማኖቱ ውስጥ ይህን አገልግሎት ለመስጠት ስልጣኑ የተሰጣቸው ሰዎች ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት ሃላፊነታቸውን ሲወጡ አይስተዋሉም፡፡ እነዚህ የሃላፊነት ቦታዎችን ተገን በማድረግ ከሃይማኖቱ "ጽድቅ" እና "በረከት" ከሚፈልጉ ሰዎች ብዝበዛ ሲያካሂዱ ይስተዋላሉ፡፡ በታለ በእውነት ስም ረጅም ልቦለድ ውስጥ ረድ ሠርዌ የተባለው ገጸባህሪም ሲያደርግ የሚታየው ይህንኑ ነው፡፡ የተሰጠውን የሃይማኖት ሃላፊነት ተንተርሶ በአንጓች ላይ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ ሲያካሂድ ይታያል፡፡

> "አጸደማርያም፣ አለሽ?"
>
> "አለሁ መሪጌታ" ትለዋለች
>
> "ቃሪያይቱን ፣ ሽንኩርቲቱን ፣ ቲማቲሚቱን አንድ'ጋ ጎረድ ጎረድ አድርገሽ ለየንታ ላኪልኝማ" ይላል፡፡ አባቱን የንታ እያለ እንደሚጠራ በኋላ ተረዳሁ፡፡
>
> <u>እናቴ ለማንም ከማታቀምሰው ጉልት ተቀምጣ ከምትሰራው የአደባባይ ወጧ ጨምራ ትልክለታለች፡፡ </u>(ታለ በእውነት ስም ገጽ ፣ 16) አጽንኦት ተጨምሯል፡፡

ይህ ሁሉ እንክብካቤ የሚደረግለት ሃይማኖትን ተገን በማደረግ ነው፡፡ ምግብ ብቻም አይደለም ሌላም ሌላም ጥቅሞች ይደረግለታል፡፡

> "አጸደማርያም፣ አለሽ?"
>
> "አለሁ መሪጌታ" ትለዋለች እናቴ፡፡
>
> "የቤት ኪራይ መቼ ነው ንገሪኝና የንታ ሲመጡ እንዲያስታውሳቸው…"

> "አ-ዬ፣ እስዎ ዳይት መድገምና ጸበል መርጨት ከጀመሩ ወዲህ የተስተካከለው ብዙ ነው። እሱ ምን ያውጣና የተቀመጡበትን ልቀበል ይተው አያስቸግሯቸው…" (*ታለ በእውነት ስም* ገጽ ፣ 18)

ብዙውን ጊዜ ረድ ሠርዌ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላትን ያጠናል። በሚያጠናበት ጊዜ በቤተ ክህነት ትምህርት እንደለመደው ቆሞና ነጠላውን አጣፍቶ ነው። የታለ እናት ግን ጸሎት እያደረገ እንደሆነ በማሰብ የምትሰራውን ስራ ትታ ቆማ ትከታተለዋለች። በሚጨርስበት ወቅት አቡነ ዘበሰማያት ደግሞ መዝገበ ቃላት የሚያጠናበትን መጽሃፍ ያሳልማታል(*ታለ በእውነት ስም* ገጽ17)።ይህን ሳደረገበት ነው ከአንጓች ጉልት ተቀምጣ ከምትሰራው የተመርጠ ምግብ አልፎም የቤት ኪራይ ብር በመተው ድጎማ የሚደረግላቸው። እንዲህ ያለውን ነው ማርክስ "ሃይማኖት የመበዝበዣ መሳሪያ ነው ፤ ስራ ጠል የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሰራተኞቹን ምንዳ አስፈራርተው የሚቀራመቱበት ፣ አላማው ከምድርና ከቁሳቁስ እንቶ ፈንቶ የማያልፍ ተራ ማታለያ ነው"(Tyson, 2006 :59) ሲል የሚናገረው። ረድ ሰርዌ ይህን መሰል ስልት በመጠቀም ነው ከአነጓች ጥቅማ ጥቅም የሚያገኘው። በርግጥ እንደ አንጓች በእምነት ለተቀበለው ሃይማኖት የሽክም ማሳረፊያ ነው(ገጽ 17)። በእምነቷ የምታገነውን ስነልቡናዊ እርካታ እንጅ የሚደርስባትን የኢኮኖሚ መበዝብዝ አስታውላው አታውቅም። ለዚህ ነው ማርክስ "ሃይማኖት ሰዎችን እንዲያንቀላፉ የሚያደርግ አደንዛዥ እጽ ነው" ሲል የሚናገረው።

በአጠቃላይ *በአጥቢያ* እና *ታለ በእውነት ስም* በተሰኙት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ሰዎች ሃይማኖትን እንደማረፊያ በማየት እና በምናባቸው ዘላለማዊ ህይወት አለ ብለው በማሰብ ዛሬን ተጽናንተው ቢኖሩም እንኳን ይህን እንደመጠቀሚያ በመውሰድ ሳይሰሩ እየበሉ ሰርቶና ለፍቶ የሚኖረውን የህብረተሰብ ክፍል የሚበዘብዙ (እንደነ ረድ ሠርዌ ያሉ)አካላት መኖራቸውን አሳይተዋል።

### 3.2.2 ስርአተ ፆታ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች

ስርአተ ጾታ(gender) ተፈጥሯዊ ከሆነው ስነ ህይወታዊ የጾታ(biological sex) ልዩነት በመነሳት "ወንድ/ሴት" የሚለውን በተለየ መልኩ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ "ሴትነት" እና "ወንድነት" ብሎ በመከፋፈል የተለየ ማህበራዊ ማንነቶች ፣ ኢኮኖሚካዊ እና ባህላዊ ውክልናዎች በመስጠት የሚመሩበት ስርአት ነው። በዚህ ስርአት ሴቶች ከወንዶች በተለየ መልኩ ይታያሉ። በሴቶች እና በወንዶች መካከል የስራ ክፍፍል፣ የአነጋገር ፣ የአረማመድ ፣ የአመጋገብ ፣ የመዋያ ቦታዎች የመሳሰሉት ልዩነቶች እንድኖሩ በማህበረሰቦች ህግ ይደነገጋል፡

፡ በዚህም የተነሳ ወንዶች ጠንካራ ሴቶች ደካማ ፤ ወንዶች ሁሉን ነገር መስራት የሚችሉ እና በአደባባይ የሚውሉ ፤ ሴቶች ግን የልጅ አሳዳጊዎችና የቤት እመቤቶች እንደሆኑ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ይህ የስርአተ ጾታ ልዩነት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ህብረተሰቦች በስምምነት የሚያወጡት ነው፡፡ በማርክሲስቶች እይታ ይህ የስርአተ ጾታ ልዩነት ሴቶችን "ማንኛውንም ስራ መስራት አይችሉም" በሚል አስተሳሰብ በኢኮኖሚ ተጨቋኝ/ተበዝባዥ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶች አንድም በመደብ ውስጥ በኢኮኖሚያዊ ስርአቱ ባለው የመደብ ክፍፍል በካፒታሊስቶች ሲበዘበዙ በሌላ በኩል ደግሞ በአባዊ ስርአቱ ተበዝብዘዋል የሚል በማርክሲስት ሴቶች የሚነሳ የእኩልነት ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ክፍል ይህ እሳቤ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ስራዎች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ የሚዳሰስበት ነው፡፡

በ*አጥቢያ* ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያለውን የስርአተ ጾታ ሁኔታ ስንመለከት በወንዶች የበላይነት ጭቆና/ብዝበዛ የደረሰባቸው ሴት ገጸ ባህሪያት እናገኛለን፡፡ *በአጥቢያ* ረጅም ልቦለድ ውስጥ እርጥባን እና የሙሉጌታ እህቶች በሴትነታቸው ሲጨቆኑ ይታያሉ፡፡

Madsen (2000) እንደምትለው ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ሴትነትን ከካፒታሊዝም ፣ ከአባዊ ስርዓት እንዲሁም ከመደብና ጾታዊ ጭቆና ከሚሉ መሰረታዊ የቅራኔ ሃሳቦች የተዋቀረ ነው፡፡ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ በመደባዊ ጥናትና በጾታዊ ትንተና ውህደት የተፈጠረ ነው ትላለች፡፡

ይህን አስመልክቶ Eagleton (2002 ፡ xii) "ማርክሳዊ ትችት ሴቶች ከወንዶች ጭቆና እና ብዝበዛ ለመላቀቅ በሥነጽሁፍ ውስጥ የሚያደርጉትን ትግል ይመለከታል፡፡" ይላል፡፡ *በአጥቢያ* ረጅም ልቦለድ ውስጥም የምናየው ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ነው፡፡ እርጥባን የቤቱ(የታፈሰ) ብቸኛ ልጅ ናት፡፡ በምትኖረው ኑሮ(በኢኮኖሚ) ከሌሎች ሴት ጓደኞቿ የተሻለች ብትሆንም "ሴት" በመሆኗ ግን ከአባቷ ማግኘት የምትፈልገውን እና የሚገባትን እንዳታገኝ በአባቷ ስትከለከል ይታያል፡፡

> ሃሳብ ተጫጭኖኝ ከአልጋዬ ተነሳሁ፡፡ እንዲህ አይነት ስሜት ሲያድርብኝ አባቴ እድሜ ላይ ሩጭሮ የደረስኩበት ያህል እኩያነት ይሰማኛል፡፡ የወትሮው ባህሪዬ እንደደመና ተገፎ ግጥጥ ያለ እውነት ግንባሬ ላይ ይወጣል፡፡ ይህን የአዘቦት ባህሪዬን አባቴ በዘዴ ያልፈዋል፡፡ አብዛኛኛውን ጊዜ ከተጫጫነኝ ሃሳብ የሚያወጡኝ የአነጋገር ፈሊጦች አሉት፡፡

<u>"ከአባት ጋር መፋጠጥ ለሴት ዝንጀሮ ማን ሰጣት!? የወንድ ዝንጀሮ ድርሻ ነው"</u>

> ንግግሮቹ ድንገተኛና ያልተጠበቁ ስለሚሆኑ የእውነቴን ጨረሮች አቅጣጫ ይስታሉ፡፡ ሳልወድ በግድ ቧልታዊ ንግግሩን የማመናተል ባተሌነት ይጠናወተኛል(አጥቢያ ገጽ 9)፡፡ (አጽንኦት ተጨምሯል)

እርጥባን ምንም ነገር ለማድረግ ከአባቷ ጋር የሃሳብ ልውውጥ ማድረግ እንደማትችል ያስገነዝበናል፡፡ የምትናገረው እውነታ ቢኖራት እንኳን "ሴት" በመሆኗ ብቻ ይህን እውነት እንዳታወጣው ትገደዳለች፡፡ ምክንያቱም "ወንድ" እንጅ "ሴት" ልጅ ከአባቷ ጋር እንደፈለገች ቃል መለዋወጥም ይሁን አባቷን በሃሳብ መጋፈጥ አትችልም የሚል የማኅበረሰብ ህግ ስላለ ነው፡፡ ሴቶች በወንዶች የበላይነት በሰፈነበት ማኅበረሰብ ውስጥ ምንም ነገር የማድረግ ነጻነት/ መብት የላትም፡፡በዚህ ውስጥ በአንድም በሌላም መንገድ ማኅበራዊ ስርዓቱ ባስቀመጠው የስርአተ ጾታ ልዩነት የእርጥባንን ተጨቋኝነት ያሳየናል፡፡ Bengsten (1977) እንደምትለው ሴቶች የበታች ተደርገው ስለሚታዩ በካፒታሊዝም ስርአት ውስጥ በጥቃቅን ስራዎች የሚሳተፉ ቡድኖች ናቸው፡፡ ትልልቅ ስራዎችን የመምራት አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ የመሳተፍ እድሉ ተነፍጓቸዋል፡፡ ትላለች፡፡ በዚህም በኢኮኖሚ ስርአቱ ሴቶች የበታች ይሆናሉ፡፡ ይህም ለብዝበዛ ያጋልጣቸዋል ማለት ነው፡፡ እርጥባንም ሴት በመሆኗ አባቷ ካለው የሃብትና የእውቀት ማማ ላይ እንዳትደርስ ሲገድባት ይስተዋላል፡፡ ይህም እየቆየ በአባቷ ታዛዥና ተበዝባዥ ሊያደርጋት እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ ይህም Madsen(2000) ማርክሲስቶች ካፒታሊዝምን የሚመለከት የጾታና የኢኮኖሚ አለመጣጣም ይከሰታል ይላሉ ትላለች፡፡ በዚህ ጊዜ የሴቶች አንጨቆንም ባይነት ይነሳል፡፡ ይህም ክስተት ከመደብ ትግል ጋር ይዛመዳል፡፡

ሌላው በዚህ ልቦለድ ውስጥ ከጾታ ጋር በተያያዘ የሚደርሰው ተጨቋኝነት በሙሉጌታ እህቶች ላይ የሚደረገው ነው፡፡ የሙሉጌታ አያት ከሴት የልጅ ልጆቻቸው አስበልጠው ሙሉጌታን ይወዱታል ወይም የተለየ ትኩረት ይሰጡታል፡፡ይህንንም እራሱ ሙሉጌታ እንድህ ሲል ይናገራል፡-

> …ሁልጊዜም ከኮዳዋ ላይ የምትተርፈው ግማሽ ብርጭቆ ጠጅ የኔ ናት፡፡ ከዚህ በኋላ ሻይ በአበሻ አራቂ ጠጥቶ ነው የሚተኛው ሬዲዮ ከፍቶ እያዳመጠ የጠጣውን ሻይ ባረቁ ከግማሽ ትንሽ ዝቅ ሲል በማንኪያ የሚጠጣበትን ትልቅ የቻይና ሸክላ ሲኒ ያንኳኳል፦
> "ቂጭል!"
> በዚህ ሰዓት ካለነው ከሶስታችን ተሽቀዳድመን መቀበል ነው፡፡ እኔ በሴቶቹ ከተቀደምኩ አሳሬን አየሁ፡፡ **"ፊዛዛ! በሴት ትቀደም? አፈር ብላ!"** ከቀደምኩ ደግሞ እራሴን እየደባበሰ እግሩ ስር አግዳሚው በርጩማ ላይ ቁጭ ብዬ በክብር እጠጣለሁ፡፡ **"ጎሽ ልጄ! የታባታቸውና ደግሞ ሴቶች ይቅደሙህ?"** (አጥቢያ ገጽ 90)(አጽንኦት ተጨምሯል)

Madsen (2000) እንደምታስረዳው በመደብ የተከፋፈለ ማህበረሰብ የሴቶች ጭቆናን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ግለሰባዊ እና ባህላዊ ማንነቶች እነደ ርእዮተ ዓለም ውጤት ተደርገው ይታያሉ፡፡ የሴቶች ንቅናቄ አራማጆች ከካፒታሊዝም ስርዓተ ማህበር ጋር ቅራኔ ውስጥ የሚገቡት የሴቶችን አቅም ዝቅ አድርጎ በማየቱ ነው፡፡ በልቦለዱ ውስጥ እንደተገለጸው የሙሉጌታ አያት በሴቶች መቀደምን እንደውርደት ነው የሚቆጥሩት፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በማህበራዊ ስርአቱ ውስጥ ሴት የበታች ተደርጋ የምትቆጠርበት ስርአት በመኖሩ ነው፡፡ በዚህም አመለካከታቸው በሴት የልጅ ልጆቻቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድሩባቸዋል፡፡ ሙሉጌታ በሚቀድምበት ጊዜ ደግሞ ይበረታታል፡፡ ይህም እንደማርክሲስቶች አተያይ የመደብ ክፍፍል ሚናን በመተካት ስርአተ ጾታ ላይ በማተኮር ሴቶችን የቤት ውስት ተግባራት ፣ የቤት ውስጥ አስተዳደርና የመሳሰሉትን እንድያከናውኑ በማድረግ በስልተ ምርት ላይ ብዝበዛ እንድካሄድ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡ በዚህ ልቦለድ ውስጥም እርጥባነና የሙሉጌታ እህቶች(ስማቸው አልተጠቀሰም) ሴት በመሆናቸው የሚደርስባቸውን ጭቆና እንድንመለከት አድርጎናል፡፡

ሌላው በፍቅር ስም በተሰኘው ልቦለድ ዋና ገጸ ባህሪው ታለሰው/አላዛር ከበርካታ ሴቶች መካከል በመኖሩ የሴቶቹን ባህሪ ተላብሶ የቀረበበት ልቦለድ ነው፡፡ ለዚህም ባህሪው "ሴታሴት" የሚል ተቀጽላ ስም ተሰጥቶታል፡፡ የሱ ታላቅ የሆነችው ቻይና ከእሱ በተቃራኒው "ወንዳወንድ" የሚል መጠሪያ አላት፡፡ እሱ ደግሞ "ሴታሴት" የሚል መጠሪያ አለው፡፡ ታለሰው ምንም እንኳ ወንድ ቢሆንም የሴትነት ጸባይ በማሳየቱ ይናቃል ፤ ከወንዶች ዝቅ ተደርጎ ይታያል፡፡ ሴቷ እንኳ ቻይና ሳትቀር ሴትነትን እንደ መሰደቢያ ስትጠቀምበት ይስተዋላል፡፡ "ሂሽ ሴታ ሴት!" ትለኛለች (በፍቅር ስም ገጽ 21)ይላል፡፡ ስትምል እነኳ "ሴታ ሴቱ ይሙት!"(በፍቅር ስም ገጽ 25)እያለች እንደምታሾፍበት ይናገራል፡፡ ይህን ጊዜ <u>**እንደሚያለቅስ**</u> ይናገራል (ገጽ 25)፡፡ (አጽንኦት ተጨምሯል) ታለ "ሴታ ሴት" በመባሉ ለምን አስለቀሰው? ከተባለ Palmisano (2001:267) እንደሚሉት *ሥርዓተ ጾታዊ ማንነት ሙሉ በሙሉ ግለሰባዊ ምርጫ አይደለም፤ የባህል ጫና ባረፈባቸው በሥርዓተ ጾታዊ ሚናዎች፣ በደንቦች እና በማኅበራዊነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ራሳችንን ወንድ ወይም ሴት ብለን ለመወሰን ያደግንበት ባህላዊ አስተሳሰብ ወሳኝ ነው፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ባህል የየራሱ የሆነ የሥርዓተ ጾታ አስተሳሰብ አለው፡፡* ስለዚህ ታለሰው/አላዛርም በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ለሴት የሚሰጠው ውክልና ከወንዶች ያነሰ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው፡፡ ይህንንም አባቱ ለሴት ልጆቹ ከሚሰጠው ግምት መረዳት

ይችላል፡፡ አባቱ(ብዜን) ሴቶች ልጆች ሲወለዱ ደስተኛ አልነበረም፡፡ ታለ ሲወለድ ግን ከደስታው ብዛት የተነሳ የጋሽ ተገኜን ጠመንጃ ነጥቆ እነደተኮሰ ተገለጿል(ገጽ 8)፡፡ ብዜን ይህንን ያደረገው አንድ ልጅ በመሆኑ ሳየሆን "ወንድ" በመወለዱ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያነት የሴትን ዝቅተኛነት በመንገር ከእናቱ እና ከእህቶቹ ሊለየው ይጥራል፡፡

"የሴት ጠባይ ለወንድ **<u>ነውሩ</u>** ነው፣ ጣ! የሴት ውሎ ለወንድ **<u>ውርደቱ</u>** ነው ጣ!" …እነርሱም ቢሆኑ ወንድ ልጅ ጸባያቸውን ሲወርስ **<u>ይንቃሉ</u>**፡፡ … አይምሰልህ ጣ! **<u>ቆፍጠን</u>** ሲል ነው እንጅ…"(ገጽ 41) (አጽንኦት ተጨምሯል)፡፡ እነዚህ አጽንኦት የተሰጣቸው(ነውር፣ ውርደት እና ንቀት) በሴትነት ውስጥ ተካተው የተገለጹ ናቸው፡፡ የ"ሴት" ጸባይ እነዚህን እንደሚመስሉ ይናገራል፡፡ በተቃራኒው የ"ወንድ" ጸባይ ደግሞ "ቆፍጣ"ናነት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ መለዮዎች ሴት ወይም ወንድ በመሆን የሚገኙ ሳይሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ በወጣው የስርአተ ጾታ ህግ መሰረት የተደንገጉ ናቸው፡፡

ታለሰው/አላዛርን የሴትነት ጸባዩ እንደሚያመዝን ከቻይና እና ከአባቱ(ብዜን) በተጨማሪ ሲፈን ትደግምለታለች፡፡

> **<u>"የወንዶች ስራ</u>** ካለ አግዝ ይሄ የሴቶች ስራ ነው፡፡"…
>
> "ሊጡን መሸብለል አይደል? ከዚያ መለስ ቀለስ እያደረኩ መቁረጥ…"
>
> "ለምን ወንድ ለመሆን አትደፍርም? **<u>ለምን እነሱ የሚያደርጉትን አታደርግም? ለምን እነሱ የሚውሉበት አትውልም</u>**?…" (በፍቅር ስም ገጽ 64)(አጽንኦት ተጨምሯል)

እንደተገለጸው ታለ ሴቶች ዳቦ ቆሎ በሚቆርጡበት ጊዜ ልቁረጥ በማለቱ ነው ይሄ የተነገረው፡፡ በስርአተ ጾታ ውስጥ የሴትና የወንድ ተብሎ የተከፋፈለ የስራ ድርሻ በመኖሩ ነው ሲፈን ይህንን ልትልው የቻለችው፡፡ ሌላው በዚሁ ምልልስ ውስጥ "እነሱ" እያለች ሲፈን የጠቀሰቻቸው አሉ፡፡ ይህም አንተ ከበርካታ ወንዶች የተለየህ ነህ ፤ ወንዶች የሚውሉት ከሴቶች ተለይተው ነው ፤ ደፋር ናቸው ፤ የሚሰሩትም ስራ የተለየ ነው፤ ስለዚህ ወንድ ሁን ለማለት ይመስላል፡፡

ከዚህ በኋላ ታለ "በፊት ቻይና ከዛም አባዬ አሁን ደግሞ ሲፈን እኔ ላይ ያዩት ምንድን ነው?" ሲል እራሱን ይጠይቃል፡፡(በፍቅር ስም ገጽ 64) ከዚያም ቻይና ጋር በመሆን "ወንዳወንድ"ነትን መለማመድ ይጀምራል፡፡ የወንድ አረማመድ እና አነጋገር ሳይቀር ለመደ፡፡ ከዚህ በኋላ ታለሰው "ወንዳወንድ" ሆኖ ያያል፡፡ ወንዳወንድነትን በለመደ ወቅት ከቤት ወጥቶ ወንዶች ከሚውሉበት

መዋል ይጀምራል። ይህ ባይሆንና ወንዳወንድነትን በቻይና አማካኝነት ባይለማመድ ልክ እንደእህቶቹ በሴትነት ጸባዩ ይቀጥላል፤ የጓዳ ስራዎችን ይሰራል፤ የእህቶቹን ልጆች በማሳደግ ጭምር ቤተሰቡን ያገለግላል ፤ ልክ እንደ እህቶቹ የጉልበት ብዝበአ እየደረሰበት ይኖራል። ይህ የስራ ድርሻ ለሴቶቹ የተሰጠ በመሆኑ ወንዶች ሲሳተፉበት እንደ ንቀትና ውርደት ይቆጠራል። በእነብዜን(የታለ አባት) ቤተሰብ ውስጥ ያሉት ሴቶች የሚያደርጉት ይህንን ነው። በዚህ የኑሮ ሂደት እየኖሩ ቢበዛ አግብተው ፈተው ልጅ ያለአባት ካመሳደግ ውጭ የሰሩት ስራ የለም። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የስርአተ ጾታ ህግ እንደነዚህ መሰል ተጽዕኖዎችን በማድረስ በሴቶች ላይ ብዝበዛ ሲያካሂድ ይታያል።

እንዳጠቃላይ በታለሰው እና በእህቶቹ ምካከል ያለው የስራ ክፍፍል ፣ የአኗኗር ሁኔታ “ሴታ ሴት” ሊያስብለው የቻለው የተፈጥሮ ጉዳይ ሳይሆን በማህበረሰቡ የወጣው የስርአተ ጾታ ድንጋጌ ነው። እንደዛ ባይሆን ኖሮ ታለ ወንድ እንደመሆኑ መጠን ሲፈጠር “ወንዳወንድ” ሆኖ ይፈጠር ነበር። በኋላም በልምምድ አያገኘውም ነበር። በመሆኑም ይህ የስርአተ ጾታ ክፍፍል ሴቶችን በመደብ ውስጥ ከመጨቆናቸው በተጨማሪ ተጨቋኝ እንድሆኑ አዲርጓቸዋል ይላሉ ማርክሲስቶች።

### 3.2.3 ቁስ አካላዊነት በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች

የማርክሲዝም ታዋቂው ርዕዮተ ዓለም ቁስ አካላዊነት እንደሆነ ተመልከተናል። ማርክስ ስለቁስ አካላዊነት ሲናገር በካፒታሊስቶች የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ ዋነኛ ትኩረታቸው ቁስ ሲሆን አንድን ነገር ወይም ሰው ከሚያወጣው ነገር ጋር ያዛምዳሉ። አንድን ሰው ልክ እንደቁስ ምን ያህል ያወጣል ወይም ያመርታል? ብለው ይገምታሉ (Tyson, 2006:62)። የማርክስም ትኩረት ይህ የካፒታሊስቶች እሳቤ እንዴት ወደ ሶሽያሊስት እሳቤ መቀየር እንዳለበት ነበር። ይህ ሰዎችን በሚያወጡት ዋጋ መለካት የማይኖርበትና የመደብ ልዩነት የሌለበት ማህበረሰብ መፍጠር ዋነኛ አላማው ነበር (Tyson, 2006:62)። ይህ የቁስ አካላዊነት ርዕዮተ ዓለም ተብሎ የተነሳውም በልቦለዶቹ ውስጥ ይህ እሳቤ እንዴት እንደቀረበ ለማሳዬት ያለመ ነው።

ቁስ አካላዊነት የሚለካው ከሀሳባዊነት ጋር ባለው ንጽጽር እንደሆነ ተመልክተናል። በመሆኑም ቁስ አካላዊነት ነገሮችን ከሀሳባዊነት ይልቅ በቁስ(ተጨባጭ በሆኑ ነገሮች) መለካት ነው። በመሆኑም ቁስ አካላዊነት በ “አጥቢያ” ረጅም ልቦለድ ውስጥ ታፈሰ በተሰኘው ገጸ ባህሪ ላይ ተንጸባርቆ ይገኛል። ይህም እንዲህ ተቀምጧል፦

"እኔ አባቴን የረታሁት ትምህርቴን ሙጥኝ በማለቴ ጠንካራ ሰራተኛ በመሆኔ ነው፡፡ እንደምታውቂው ፤ በመካከል ድንገት የወለደኝ ስለነበርኩ ካደኩ በኋላ ነው ቤተሰቡን የተቀላቀልኩት፡፡ በዚህ ላይ ከትዳሩ ውጭ ወስልቶ ስለወለደኝ እኔን ማየት ወቀሳ ነበር የሚሆንበት፡፡ <u>ያም ሆኖ በስተመጨረሻው ዘመን ብቸኛው መመኪያው እኔ ሆኜ ነበር፡፡ የተቀሩትን ልጆቹን በሰበብ ባስባቡ ከሀብቱ ላይ ገለል ሲያደርጋቸው የነበረው እኔ ጠንካራ ሰራተኛና የተማርኩ መሆኔ ስለረታው ነበር</u>፡፡ እሱ በሚስጥር ያስቀመጠልኝን ሀብት የማካካሻ ክፍያ አድርጌ ነው ድርጅቱን ከውርስ መቀራመት ያዳንኩት፡፡ <u>ይህን ሁሉ ያደረኩት የአባቴ ልጅ በመሆኔ ብቻ አይደለም፡፡ በማወቄ ፣ በመማሬና በጠንካራ ሰራተኛነቴ ነጥቄ ያስቀረሁት ነው</u>"(አጥቢያ ገጽ 11)፡፡(አጽንኦት ተጨምሯል)

ታፈሰ እንደሚለው የአባቱን ሀብት ያገኘው "ልጅ" ስለሆነ ብቻ እንዳልሆነ ነው፡፡ ሀብቱን ለማገኘት ያስቻለው ጠንካራ ሰራተኛ በመሆኑና በመማሩ እንደሆነ ነው የሚገልጸው፡፡ ስለዚህ "ልጅነት" ብቻውን ከ "አባት" መገኜት ያለበትን ክብር ፣ ጥቅምና ዝነኝነት ማግኘት አይቻልም የሚል ጠንካራ እምነት አለው፡፡ ለዚህም ነው እርጥባንን "...ከእኔም ጭምር ነጻ ለመውጣት መማር አለብሽ"(አጥቢያ ገጽ 11) ሲል የሚያስጠነቅቃት፡፡ ለታፈሰ የ "አባትነት" እና የ "ልጅነት" ትስስር ከቁስ ጋር ብቻ የተያያዘ ነው፡፡ ለቁስ ያለው ግምትም ከፍ ያለ ነው፡፡ እርጥባን ይህንን አመለካከቱን በምትረዳበት ጊዜ አባቷ ከሀብት በቀር ለምንም ነገር እንደማይጨነቅ ትናገራለች፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወድህ የተረዳሁት የአባቴ እንከን ይሄ ነው፡፡ <u>የሕይወትን ግብ ከሀብት ጋር ብቻ ማላጠፍ፡፡ የኑሮ ፣ የደስታ ፣ የበላይነትና የአሸናፊነት ልኬቱ በሱ ቤት ሀብት ብቻ</u> **ነው**፡፡ ሀብትን በሚያንቋሽሹና በሚያሳንሱ ክርክሮች ላይ አይታደምም፡፡ ከታደመም ፊቱ ተለዋውጦ ኃይለ ቃል ይናገራል፡፡ <u>**"ሀብትን ዋጋ ቢስ አድርጎ የሚቆጥር ሰው መጋኛ ብቻ ነው፡፡"**</u> ይላል፡፡ ለዚህ ይሆናል ደጋግሞ የጥንት ጓደኛውን ፣ የእኔን አስተማሪ ዶክተር ማርቆስን <u>"ያ መጋኛ ደህና ነው?"</u> እያለ የሚጠይቀኝ(አጥቢያ ገጽ 11)፡፡ (አጽንኦት ተጨምሯል)

ታፈሰ ለቁስ ያለው ግምት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለሀብት ዝቅተኛ ግምት ያላቸው ሰዎች ለሱ ከሰውነት የወረዱ ናቸው፡፡ እነዚህንም "መጋኛ" ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከልጅነት ጓደኛው ከዶክተር ማርቆስ ጋር ተቃራኒ ናቸው፡፡ ማርቆስ የሶሽዮሎጅ ትምህርት ያጠና ነበር፡፡ ከታፈሰ ጋር ያለው አመለካከትም ተቃራኒ ነው፡፡ ይሄ ጉዳይ ደግሞ ለታፈሰ አይዋጥለትም፡፡ በሁለቱ መካከል ያለውን ቅራኔ ዶክተር ማርቆስ እንድህ ሲል ያስቀምጠዋል፡፡

... "አባትሽ ወጣት እያለም ደሃ ይጠላ ነበር፡፡ ሀብትን ለሰው ልጅ እንደ አንድ አስፈላጊ አካሉ ይቆጥረዋልና ድሆችን 'በፈቃዳቸው ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች' እያለ

እስከመሳደብ ይደርሳል። ሳር ቅጠሉ ኮሚኒዝምን በሚያንቆለጳጽስበት በዚያ ዘመን እንኳ ብቻውን አንድ ጎራ ይዞ ይከራከር ነበር" በቦዙ ዓይኖቻቸው ያለፈ ዘመን ለመጥራት ትንቅንቅ ይገጥማሉ።

"ብዙ የኮሚኒስት አፍቃሪ ወጣቶች እሱን ለመግደል ይፈልጉ ነበር። ንግግሩ አበሻቃጭ ስለሆነ የተቀደሰ ሃሳብሽን መጥፎ ሽታ ሰጥቶ ለውሻ የሚጣል ያደርገዋል። እኔንማ ማርቆስ ብሎ ጠርቶኝ አያውቅም። ማርክስ ነው የሚለኝ። ይሄንን ወደፊት በሰፊው አጫውትሻለሁ" (አጥቢያ ገጽ 27)።

ከአርጥባን እና ከዶክተር ማርቆስ ንግግር የምንረዳው ታፈሰ ከምንም ነገር ቁስን እንደሚያስቀድም  እና ለቁስ ልዩ ትኩረት እንዳለው ነው። ይህም የቁሳዊነትን እሳቤ የሚያመላክት ነው። ማርክስም ስለቁሳዊነት የተናገረው ይህንኑ ነው። " የምንኖርባት ዓለም የተገነባችው በቁሳዊነት ነው ፤ እኛነታችንም ቁሳዊ ነው፤ ማንነታችንም የሚቀረጸው ከቁስ ነው"(Dobei, 2012 : 90)። ለታፈሰ "እኔ" እና "ገንዘብ" የሚሉት ሁለት ነገሮች እጅጉን አስፈላጊ ናቸው።ከዚህ ጋር በተያያዘ "ኮምሬድ" የተባለውም ገጸ ባህሪ ይህንኑ አመለካከት ሲያንጸባርቅ ይታያል። ኮምሬድ "እውቀቴን ወደ ገንዘብ ቀይሩልኝ" በማለት ቁሳዊነት ከሃሳባዊነት እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ሲናገር ይሰማል። በዚህ ወቅት ከእውቀት ይልቅ ገንዘብ ተጨባጭና የሁሉ ነገር ማንቀሳቀሻ ኃይል እንደሆነ ለማስረዳት ይጥራል።

"እውቀቴን ወደ ገንዘብ ለመለወጥ ነው የመጣሁት"

"ጥሩ! ምን አዲስ እውቀት አለህ?" እያለ ወደ መንገድ ዳር ይዞት ወጣ። ከስሜቱ መገላገያ ሰበብ አድርጎ ተቀብሎታል ስል አሰብኩ።

"ስለ ሰው" አለ ኮምሬድ።

"ጥሩ! ሰው ምንድን ነው?"

<u>"ሰውማ ሸቀጥ ነው። ተነጻጻሪ ልውውጥ ይኖረዋል</u>(አጥቢያ ገጽ 38)።(አጽንኦት ተጨምሯል)

"ሰው ሸቀጥ" ነው በሚለው ሀሳብ "ሰው" ለብቻው(ሰው በመሆኑ ብቻ) ዋጋ እንደሌለው ያሳያል። ሰው ሰው የሚሆነው የሆነ ዋጋ ሲያወጣ ነው። ካልሆነ ግን ሰውነት ብቻውን ዋጋ የለውም። ሰዎች የሚለኩት በሚያወጡት ዋጋ ከሆነ ምንም ዋጋ የማያወጣ ሰው አስፈላጊ አይደም። የሚል አመለከከትን የሚያራምድ ነው። ይህንንም ኮምሬድ እንድህ ሲል ያስረዳል፦

"... ከዱር ያለከልካይ ሄደህ ከምትለቅመው አቃቅማ ይልቅ የጓሮ ጎመን ዋጋ አለው።" በድባባማ ብርሃን ውስጥ እድፍ የተለደፈበት ፊቱን አየሁት። ንግግሩ በስሜት የታጀበ

> አይደለም። "የጎሮ ጎመን ከዱር ፍሬ በላይ ዋጋ የሚኖረው ጊዜና ጉልበትህን ስላፈሰስክበት ነው። ሰውም እንደዚያ ነው። እንደ ዱር ፍሬ፣ ወፍ እንደዘራው የሚበቅል ፣ ምንም እውቀት ያልፈሰሰበት የሰው አቃቅማ አለ። ከዚህ ሰው ይልቅ የኔታጋ የተማረው እንደ ጎሮ ጎመን በጥቂት እውቀት ላይ የተመሰረተ ጉልበትና ጊዜ የፈሰሰበት ሰው የተሻለ ዋጋ አለው። እነዚህ ሁለት ሰዎች በንጽጽሮሽ ልውውጥ ገበያ ቢወጡ <u>**የአምስት ቁና አቃቅማ ዋጋ አንድ ነጠላ ጎመን ብቻ ሊሆን ይችላል።**</u> እንድያ ነው ሰው ሽቀጣዊ ባህሪ አለው።" ያብሰለሰለ መስሎ ቀጠለ…
>
> "እኔ በራሴ ካፈሰስኩት እውቀት ውጭ ነጥለህ ከተመለከትከኝ አርባ አምስት ኪሎ ስጋና አጥንት ብቻ ነኝ። በቃ! ሊያውም ስለማይበላ ጠያቂ የሌለው ለመግማትና ለመበስበስ የተዘጋጀ 45 ኪሎ ስጋና አጥንት" (አጥቢያ ገጽ 38- 39)(አጽንኦት ተጨምሯል)

እንደ ኮምሬድ አነጋገር ሰው እውቀት ከሌለው ወይም አንድን ሰው ለመስራት የሆነ ኃይል ወይም ገንዘብ እስካልወጣ ድረስ ርካሽ ይሆናል ፤ ዋጋ የለውም የሚል ነው። ድህነት የሚስፋፋውም በዚህ ምክንያት ነው የሚል የማርክሲስቶች ርዕዮተ ዓለም አለ። የእሱም አነጋገር ይህንን ርዕዮት የሚደግፍና የሚያንጸባርቅ ነው። ይህን አመለካከት ሙሉጌታም ይደግፈዋል። "ድህነት ምንጩ ቀኑን ሙሉ መተኛት አይደለም። <u>**የማያስፈልግ ሰው መሆን ነው። ርካሽ ነገር ላይ ጉልበትንና ጊዜን ለማባከን መገደድ ነው።**</u> የትምህርት ፣ የእውቀት ፣ የሀብት መነሻ ሳይኖረን የጋማ ከብቶች የሚሰማሩበት የስራ መስክ ላይ ከእነሱ ጋር የመጋፋት ውጤት ነው። በምድረ በዳ በመጮህ ሰሚ አይገኝም። የምድረ በዳ ሰባኪ መሆን ነው ድህነት(አጽንኦት ተጨምሯል አጥቢያ ፤1999 ፣119)።ይህም የሚያሳየው በካፒታሊስቶች እሳቤ "ድሆች" ደሃ የሚሆኑት ስራ ባለመስራታቸው ሲሆን ሳይሰሩ መብላትም የለባቸውም የሚል አመለካከት ሲኖራቸው እንደ ማርክስ ያሉ የኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም አፍላቂዎችና ደጋፊዎች ሰዎችን ደሃ የሚያደርጋቸው አለመስራታቸው ብቻም ሳይሆን አንድም ለሚሰሩት ስራ ተገቢውን ክፍያ አለመከፈላቸው በሌላ በኩልም ፍትሃዊ የምርት መሳሪያዎች ክፍፍል ባለመኖሩ ነው የሚለውን ነው። በአጥቢያ ረጅም ልቦለድ ውስጥም እነዚህን ሁለት ርዕዮተ ዓለማዊ እሳቤዎች በሁለቱ ገጸ-ባህሪያት(በታፈሰ እና በኮመሬድ) ተወክለው ሲንጸባረቁ ይታያሉ። በእነዚህ ገጸ ባህሪያት የሚገለጹት ቁሳዊነት እሳቤዎች የሰው ልጅ ማናባዊ ከሆነው ዓለም ይልቅ ቁሳዊ የሆነ ዓለም ምን ያህል ሊያስፈልገው እንደሚችል እና የመኖር ዋስትናው የሚረጋገጠው በቁሶች መኖር እንደሆነ ማሳየት ችለዋል።

### 3.2.4 መደብ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች

ኢኮኖሚያዊ መደብ በዋናነት ቡርዧውን እና ወዝ አደሩን የሚይዝ ነው። በዚህ የመደብ ልዩነት ውስጥ በዋናነት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ ሰዎች(ፕሎሬታሪያት) በከፍተኛ ደረጃ ባሉ ሰዎች(በቡርዧ) ጭቆና ይደርስባቸዋል። ይህም ከጉልበት ብዝበዛ አንስቶ እንደሰው የማይቆጠሩበት ደረጃ እስከሚደርስ ነው። ለሚሰሩት የጉልበት ስራም ተገቢውን ክፍያ አይከፈላቸውም። በዚህም ምክንያት ዘመናቸውን ሙሉ በድህነት እንዲኖሩ ይፈረድባቸዋል። በድህነት መኖራቸው ሳያንስ ይባስ ብሎ ከሰው ልጅ እጅጉን የተለዩ ተደርገው ይቆጠራሉ። በአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ እነዚህን መሰል በኢኮኖሚያዊ የመደብ ልዩነት የተነሳ በማህበረሰቦች መካከል ያለውን መበላለጥ እና ልዩነት የሚያሳዩ ምልልሶች በዚህ ክፍል ተመልክተዋል።

አጥቢያ ረጅም ልቦለድን ስንመለከት በአራት ኪሎ አካባቢ የሚኖሩትን ማኅበረሰቦች በታፈሰ አጠራር "ድሆች" ባላቸው የኢኮኖሚ ዝቅተኛነት የተነሳ እጅጉን ጭቆና ሲካሄድባቸው የሚያሳይ ነው። ይኸው ታፈሰ የተባለው ገጸባህሪ "ሙጃ" በማለት ነው የሚጠራቸው። በታፈሰ አስተሳሰብ እነዚህ ማህበረሰቦች ከአካባቢው ተነቅለው መጣል አለባቸው። ምክንያቱም ድህነት ሊንሰራፋባቸው የቻሉት ሰነፍ በመሆናቸው መስራት ስለማይወዱ ነው ብሎ ስለሚያስብ ነው። በዚህ ልቦለድ ውስጥ ታፈሰ ቡርዧ የተባለውን የመደብ ክፍል ወክሎ ቀርቧል። Tyson (2006: 56) እንዳስቀመጠችው በዚህ የመደብ ክፍል ስር ያሉ ሰዎች አብዛኛዎቹ የገንዘብ ምንጫቸው ውርስ እንደሆነ ነው። ታፈሰም ከእነዚህ መካከል የሚመደብ ነው። በመጀመሪያ ገንዘቡን ያገኘው በውርስ ከአባቱ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ሃብቱን ተገን በማድረግ በአራት ኪሎ አካባቢ የሚገኙትን ማህበረሰቦች ቦታው "ለኢንቨስትመንት" ተፈልጓል በሚል ምክንያት ያፈናቅላቸዋል። ብሎም የእነዚህ ማህበረሰቦች መፈናቀል ያሳሰባት ልጁ(እርጥባን) ልትረዳቸው ስትፈልግ ይህን እንዳታደርግ ይከለክላታል።

> "መጥፎ ቦታን ለማቅናት ስትወስኝ የምታካሂጅው ምንጣሮ **ሙጃ** ላይ ብቻ ሳይሆን አካባቢውን መጥፎ ያደረጉ ሰዎችም ላይ ያርፋል። ይሄ ምኑ አዲስ ሆኖ ነው እንደ አንድ ማኅበራዊ ምስቅልቅሎሽ የሚቆጠረው?" አባቴ እንደተናደደ የገባው ቡቹ የአሮጌ በር ድምጽ እያሳማ መቅበጥበጥ ጀመረ። [...]
>
> "የየትኛውም ሃገር ሀብት የተከማቸው <u>በጥቂት ሙጃዎችና ድሆች መጨፍጨፍ</u> ነው። ሁለቱም የማያፈሩበትን ለም መሬት ሙጥኝ ይላሉ። ያ ደግሞ መሬት ተፈላጊ ነውና የሁለቱም ሕይወት አደጋ ላይ ይወድቃል። <u>መሬትን ለሙጃና ለድሃ መተው ጠፍ ሀገር</u>

**<u>ያስታቅፋል"</u>** አባቴ ሀብትና ደሃ ሲነሳ ለምን እንድህ የሰሉ ቃላትን እንደሚተፋ አይገባኝም(አጥቢያ ገጽ 18-19)።(አጽንኦት ተጨምሯል)

ታፈሰ ለድሆች የተለየ ጥላቻ አለው። በዚህም አመለካከቱ ሰዎችን ከሙጃ ጋር ያመሳስላቸዋል። "ሙጃ እና ደሃ ለመሬት አይጠቅሙም። ስለዚህ ተነቅለው መጣል አለባቸው።" የሚል የጸና አቋም አለው። ይህን አቋሙን ደግሞ እርጥባን ትቃወመዋለች። በዚህ ተቃውሞዋ ምክንያት እሷ ላይ ጥላቻ ያሳድርባታል።

> "ሙጃና ደሃን ምን አንድ አደረገው?" አልኩት
>
> ለጥያቄዬ መልስ ከመስጠት ይልቅ ትክ ብሎ አስተዋለኝ። ትክታው እንደብረት የማይታጠፍ ነበር። ጭንቅላቴን ከሰነገኝ ሀሳብ ድንገት ተነጥቄ የአባቴን እኩያነት ያጣሁ ሆኖ ተሰማኝ "ሙጃ ... ደሃ አታፈላስፊኝ! ያም ሆነ ይህ ከእኔ ጋር ግንኙነት ያላቸው **<u>ድሆች ሙጃዎች</u>** ጋ ሄደሽ ምንም እንድትሰሪ አልፈቅድልሽም። ከተማው በድሆች ምንጣሮ ላይ ተግቷል። ወደአንዱ ጠጋ ብለሽ ጥናትሽን ስሪ ..." ብሎ ፊቱን ወደ በሩ መለሰ። ወደፊት ከላካቸው ቃላቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ወደኂላ ቀሩ "ምን አይነት ዕዳ ..." ቦቹ አባቴን ሸኝቶ ወደኔ ተመለሰ(አጥቢያ ገጽ 19)።(አጽንኦት ተጨምሯል)

በእሱ አተያይ በኢኮኖሚ ዝቅ ያሉ ሰዎች (ድሆች) ከሰው አይቆጠሩም። ደሃ እንድሆኑ ያደረጋቸውም አላስፈላጊነታቸው ነው ብሎ ያምናል። ለዚህም ነው ከሙጃ ጋር የሚያመሳስላቸው። እነዚህ "ደሃ" የሚባሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በዋናነት ትኩረት የሚያደርጉት ስራ ከመስራት ይልቅ "ወሲብ" እና "ብዙ ልጆችን መውለድ" ላይ እንደሆነ በልቦለዱ ውስጥ(አጥቢያ ገጽ 103) ተገልጿል። በዝቅተኛ ደረጃ ያለው ማኅበረሰብ(ደሃ) ለወሲብ እጁን የሰጠ እና ልጆችን መውለድ ብቻ ስራው ያደረገ ነው የሚል የካፒታሊስቶች አስተሳሰብ አለ። ለዚህም ነው ካፒታሊስቶች በዝቅተኛ ደረጃ ያለው ማኅበረሰብ የድህነት አመንጭ እንደሆነ በመቁጠር ብዝበዛ የሚያካሂዱት(ምንም እንኳ የማርክሲስቶች አስተሳሰብ ከዚህ ተቃራኒ ቢሆን ማርክሲስቶች ድህነት የሚመጣው በደሃ ማኅበረሰቦች ችግር ሳይሆን የልዕለ መዋቅሩ የማምረቻ መሳሪያዎች አያያዝ ችግር ነው ወይም የጉልበት ሰራተኞች መከፈል የሚገባቸውን ክፍያ ስለማይከፈላቸው ነው የሚል አመለካከት ነው ያላቸው)(Tyson, 2006 : 54)። በአራት ኪሎ ያሉ ማኅበረሰቦችም የዚሁ ፀባይ የሚታይባቸው ናቸው። ይህንንም ሙሉጌታ የተባለው ገጸ ባህሪ እንዲህ ሲል ያስቀምጠዋል፦

ወሲብ የጥጋብ ውጤት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ፍጹም ስህተት! ቅንዝረኝነት የድህነት ውጤት ነው፡፡ ወሲብ በማጣት ይገናል…፡፡ አለበለዚያማ እኛ መንደር ዝር ባላለ ፣ እንደስም'ኳ´ችግር ማለዘቢያ ባልተገኘ ነበር፡፡

ወሲብ የመንደራችን ቅመም ነው፡፡ የማይገባበት ቦታ የለም! እግዚአብሄር የሰው ልጅ ችግሩን ቀብቅቦ የታሰበበት የሚያደርስ አጋሰስ ያደረገው በወሲብ ነው ያልኩት የኛን መንደር ሰዎች ሳስታውስ ነው፡፡ የሰው ልጅ ምን ያህል ቢደክም ለፍትወት የሚሆን ኃይል አያጣም፡፡ ከየትም ከየትም ብሎ እንጥፍጣፊዋን አጠራቅሞ ለዚችው ያውላታል፡፡

አንዳንድ ጊዜ መንደራችን የፍየሎች ጋጥ መስላ ትታየኛለች፡፡ በወሲብ ሁሉም እኩል ነው፡፡ ወጠጤው ከአውራ ጋር እየተጋፋ ከንፈሩን ገሽልጦ ሴቶች ጭራ ስር ይገኛል፡፡ እንደነገሩ ትዳር ያላት ጨዋ መሰል ሴት ደጅ ልትወጣ ወጣ እንዳለች ካንዱ የመንደር ጎረምሳ ጋር ተጣምዳ ትታያላች… (አጥቢያ ገጽ 103)

ተራኪው እንደሚለው በአራት ኪሎ የሚኖሩ ህብረተሰቦች ምንም እንኳ በችግር ማጥ ውስጥ የተከተቱ ፣ በቂ አልባሳት ፣ መጠለያና ምግብ የማያገኙ ቢሆኑ ለወሲብ እጃቸውን የሰጡ ናቸው፡፡ ከወጣት እስከ አዛውንት ያሉት የህብረተሰቡ ክፍሎች በዚህ የተካኑ ናቸው፡፡ ይህ ድርጊታቸውም ታዳጊዎችን ያለ እድሜያቸው የልጅ አሳዳጊዎች ብሎም ሴተኛ አዳሪዎች እንድሆኑ አስገድዷቸዋል፡፡ ይህ የኑሮ ዘይቤያቸው ከልጅ ወደ ልጅ በመተላለፉ እነሱም ተላምደውታል፡፡ እንደምንመለከተው በገጸባህሪያቱ መካከል በኢኮኖሚ መለያየት ምክንያት በሚመጡ ማህበራዊ መደቦች ውስጥ ኢፍትሃዊነትን የሚያሳይ ፣ በሰዎች መካከል የሽቀጦችና የኃይል ሚዛን አለመጣጠም ፣ ሰራተኛውን ክፍል መጨቆንና የሚደርስባቸውን ግፍ ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በልቦለዱ ውስጥ ድሆች በስም እንኳ ሳይቀር ሲለዩ ይታያል፡፡ ይህም ኢኮኖሚያዊ መደቡን አንጸባራቂ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምንም እንኳ Smith(1967) ስም እና ተሰያሚው ነገር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንደሌላቸው ቢናገርም አንዳንድ የማህበረሰብ አስተምህሮዎች ደግሞ ስም የተሰያሚውን ነገር ማንነት ፣ ስብዕና ፣ተግባር ፣ ታሪካዊ አመጣጥ ፣ የሕይወት ገጠመኝ ፣ ዘር ፣ የኑሮ ደረጃ ፣ መልክ ፣ ቁመት ፣ አገልግሎት … ወዘተ የመሳሰሉትን ነገሮች መግለጽ እንዳለበት ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአጥቢያ ልቦለድ ውስጥ ስም ሲወጣ ከሀብት ጋር ተያይዞ እንደሆነ ታፈሰ ይነግረናል፡፡ በዚህም ምክንያት ልጆች ሲወለዱ የሚሰየሙት ስሞች የወላጆቻቸውን ኢኮኖሚያዊ መደብ ገላጭ ናቸው፡፡ የልጆቻቸው ስም ብቻ ሳይሆን ሌሎች የግለሰቡ ንብረቶችም ሲሰየሙ የባለቤቱን ኢኮኖሚ ያገናዘበ መሆን እንዳለበት በልቦለዱ ውስጥ ያለው ትረካ ይነግረናል፡፡ መደብን ከሚገልጹ ስሞች መካከል ለእርጥባን ውሻ የተሰጠው አንዱ ስም እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

> አንድ ቀን ውሻውን ባወጣሁለት ስም ስጠራው ሰምቶ **<u>"ለምንድን ነው የደሃ ስም ያወጣሽለት?"</u>** አለኝ "ውሻሽኮ ያንች በሆነ ሰዓት ካለሽ ሃብት ላይ በተወሰነ መብት አለው:: ስለዚህ ከአንድ መጠነኛ ገቢ ካለው ሰው የተሻለ ሀብት ውሻሽን አውርሰሽዋል:: እንዲህ ዓይነት አኗኗር ያለውን ውሻ ደረጃውን **<u>ዝቅ አድርጎ የደሃ ስም</u>** መስጠት ተገቢ አይመስለኝም:: ቦቹ አንድ የደሃ ደቦል ስም ነው:: ሳይበላ የወፈረ ህጻን አይነት"(አጥቢያ ገጽ 16)(አጽንኦት ተጨምሯል)

እንደ ታፈሰ አመለካከት ስሞች መለያ አላቸው:: ለሃብታም ልጆች የሚወጣው ስም ለደሃ ልጆች ከሚሰጠው ስም ይለያል:: ሃብታሞች ልጆቻቸውን ሲሰይሙ ንብረታቸውን ገላጭ የሆኑ ስሞች ያወጣሉ:: ድሆቹም እንዲሁ ድህነታቸውን የሚገልጹ ስሞች ያወጡላቸዋል:: ይህ ካልሆነ ግን ስህተት ነው ማለት ነው:: አንድ ድሃ ሰው የሃብታም ልጅ ስም ቢያወጣ ተገቢ አይደለም ማለት ነው:: በዚህም የመደብ ልዩነቶች ይስተዋሉባቸዋል:: ከዚሁ ከስም ጋር በተያያዘ ኮምሬድ የተባለው ገጸ ባህሪ ያለውንም አተያይ እንመልከት፦

> "ኮምሬድ! ኮምሬድ!"
>
> ሙሉጌታ ሳያስበው ስሜቱ ለጥሪው ታዘዘ:: እንደመነሳት ቃጥቶት መለሶ ተቀመጠ:: አካባቢያችን ያሉ ሰዎች ለድምጹ ቀልባቸውን ሰጡ መሰለኝ::
>
> "ኮምሬድ"
>
> ስላላስቻለው ብድግ ብሎ መስኮቱን በመክፈት ወደውጭ አሰገገ:: ጎላ ያለው ድምጽ ለዝቦ "ኮምሬድ **<u>ስሜን አገኘሁት</u>**" አለ ጥቂት ሳቆች ከወደውስጥ ተሰሙ::
>
> "የት  አገኘሽው?" አለ ሙሉጌታ ሳቅ የሰማበትን አካባቢ በጅምላ ገላምጦ
>
> "ድሮ የሚያውቀኝ ሰው ነገረኝ:: ሀዲስ እባላለሁ:: በደስታ የአባቴን ስም ሳልጠይቀው መጣሁ::
>
> ሙሉጌታ ቁጭ ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ:: ...(አጥቢያ ገጽ 43)(አጽንኦት ተጨምሯል)

የሰው ልጆች ብዙ ነገሮችን ሊያጡ ይችላሉ:: ስም ግን ሊያጡ አይገባም ወይም ስማቸውን ሊረሱ አይችሉም:: በልቦለዱ ውስጥ የምናየው ገጸ ባህሪ ግን ስም እንኳ አጥቶ ነው የምናገኘው:: ስም ያጣውም ከድህነቱ አንጻር ነው ወይም የሚኖርበት የኑሮ ደረጃ ይህን እድል እንዲቋደስ አድርጎታል:: እሱ እንደሚለው የአባቱንም ስም አያውቅም:: ምክንያቱም የባላባት ልጅ አይደለም ፤ የሀብታም ልጅ አይደለም:: ሀብታም እና ታዋቂ ያልሆነ ሰው ደግሞ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ ስም የለውም:: በሞተ ጊዜ አብሮ የሚቀበር ስም ነው ያለው:: ታፈሰም ይህንኑ በመደገፍ ነው "ሆዱን ለመሙላት የሚንጠራወዝ ሰው ያው እንስሳ ነው፣ እንስሳ ደግሞ

ለመዝገብ የሚበቃ ምንም ታሪክ የለውም" (አጥቢያ ገጽ 21) ሲል የሚናገረው። እንደ ታፈሰ አነጋገር "ደሃ" ለመዝገብ የሚበቃ ታሪክ የለውም። ኮምሬድም ይህንኑ ነው የሚነግረን። የአባቱን ስም አያውቅም እሱም ስም የለውም። ኮምሬድ በስሙ መረሳት ውስጥ አንዳች የበታችነት ስሜትን ሲያራግብ ይታያል። ይህ የበታችነት ስሜት ከኢኮኖሚያዊ መደቡ ማነስ የመነጨ ይመስላል።በመሆኑም መደብ እነዚህን በመሰሉ ምልከታዎች ሲንጸባረቁ ይታያሉ።

በልቦለዱ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ የመደብ ልዩነቶች እነዚህን በመሰሉ ሁነቶች ይንጸባረቁ እንጅ ዋናው ጉዳይ ኢኮኖሚያዊ ሃይል ያላቸው ሰዎች ዝቅተኛውን የህብረተሰብ ክፍል ሲጨቁኑትና ሲበዘብዙት የሚያሳይ ነው። ሙሉጌታ ከመምህርነት ሙያው ከለቀቀ በኋላ በአራት ኪሎ ሲኖር ስራ ለማግኘት ተንከራቷል፤ ግን ሊያገኝ አልቻለም። ሰዎች መስራት እየቻሉ ስራው ግን ይነፈጋቸዋል። በዚህም ራሳቸውን ለብዝበዛ አሳልፈው ይሰጣሉ። ሙሉጌታንም የምንመለከተው ይህንኑ ድርጊት ሲያደርግ ነው። በመምህርነቱ ቢቀር በጉልበቱ ሰርቶ ማደር ይፈልጋል። ነገር ግን የጉልበት ስራ የሚሰጠው ሰው እንኳን ማግኘት አልቻለም።

> "ለምሳሌ እኔን እይኝ" አለኝ። በትንሽ ብር ተቀጥሬ ገጠር ሄድኩ። ማስተማር ጥሩ ነበር። ነገር ግን እዚያ ሆኜ እንኳን አያቴን ልረዳ ለራሴም አይበቃኝ። በዚያ ላይ ለአያቴ ያለኋቸው እኔው ነኝ።[...] ስራዬን ጥየው መጣሁ። ይኸው ሁለት አመቴ ስራ የለም። ከሰባት በላይ ትምህርት ቤቶች ማመልከቻዬ ላይ ተኙበት።"
>
> "ሌላው ቀርቶ ድንጋይ ለመሸከም ሞከርኩ። እጆቼን እያዩ ይመልሱኛል። <u>**በቅናሽ እንኳን እኔን ለመቅጠር ፈቃደኞች አይደሉም። እንድህ አንዳንዴ አህያ የመተካት ስራም ይነፈግሻል።**</u> ..."(አጥቢያ ገጽ 120)(አጽንኦት ተጨምሯል)

ሙሉጌታን የምንመለከተው ለመምህርነት ይቅርና ለጉልበት ሰራተኝነት እንኳ የሚሆን ስራ አለማገኘቱን ነው። ይህ የሚያመለክተው የኢኮኖሚው ስርአት እንደ ታፈሰ ባሉ ባለሃብቶች ስለሚመረና ስለሚንቀሳቀስ ዝቅተኛው ህብረተሰብ ጭቆና ፣ መፈናቀል እና ብዝበዛ እንደሚደርስባቸው ነው። ታፈሰ ምንም እንኳ አንድ ሰው ቢሆንም የአራት ኪሎን ኗሪ በሙሉ ለማፈናቀል ኃይል ሲኖረው እንመለከታለን። ይህም የሚያሳየው ኢኮኖሚያዊ የመደብ ልዩነት በህብረተሰቡ ላይ ምን ያህል ተጽእኖ ማሳደር እንደሚችል ነው። በዚህ የተነሳ በዙዎቹ መስራት እየቻሉ በማይመች የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ በመኖራቸው ለመበዝበዝ ራሳቸውን አሳልፈው ሲሰጡ ይታያሉ። <u>ሚዳቋ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለነብርም ጭምር ነው የተፈጠረችው</u>። ይህን ተፈጥሮ ደንግጎታል። (አጥቢያ ገጽ 121)።(አጽንኦት ተጨምሯል) ከሙሉጌታ ንግግር መረዳት

የሚቻለው "ድሆች" በ "ሃብታሞች" ሊጨቆኑ ፣ ሊበዘበዙና አገልጋይ እንድሆኑ የሚያስገድድ ተፈጥሯዊ ድንጋጌ መኖሩን ነው::

በአጥቢያ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በአራት ኪሎ አካባቢ በሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችና በታፈሰ መካከል ትልቅ የመደብ ልዩነት ተፈጥሮ ይታያል። ታፈሰ የቡርዧውን መደብ ሲወክል በአራት ኪሎ የሚኖሩት ማህበረሰቦች ደግሞ ፕሮሌታሪያት የሚባለውን መደብ ወክለው ተጨቋኝና ተበዝባዥ ሆነው ቀርበዋል። በተፈጠረው ኢኮኖሚያዊ ስርአት መዛባት ምክንያትም እንደ ሙሉጌታ እና ኮምሬድ አይነቶቹ የስነ ልቡና ቀውስ ሲደርስባቸው ይታያሉ።

በታለ በእውነት ስም ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያለውን የመደብ ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ የታለ እህቶች በቤተሰቦቻቸው ቤት ሲኖሩ የነበረውን የአኗኗር ዘይቤ እና አሁን ያሉበትን ኑሮ በማነጻጸር ታለ ሲናገር እናየዋለን። በዚህ ንግግሩ ውስጥ በተለያየ የመደብ ደረጃ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ያላቸውን የአኗኗር ሁኔታ ያሳያል።

> "እዚያ ሽንጣም የወላጆቻችን ቤት ውስጥ እንደአውቶብሱ ተሳፋሪ ማገሩን ይዛ እንዳላደረች..."
>
> ስስቅ አየችኝ
>
> "ምን እንዳሰብክ ገብቶኛል።" ሳቀችና "እዚያ ጋ መታጠቢያ ቤት አለ፤ ይሄኛው የአንተ ክፍል ነው። ክፍልህ ውስጥ ፎጣ አለ። ታጥበህ ስትወጣ የመቃሚያ ልብስህን እንደቢጃማ ተጠቅመህ ናፕ ማድረግ ትችላለህ። "
>
> የሚጨንቅ ነገር አለው። የኛ ቤተሰብ መታጠቢያ ቤት ሽንት ቤቱ ወዳለበት ጓሮ ዞር ብሎ ጆንያ በመጋረድ የተዋቀረ ነው። ገላ ለመታጠብ የፈለገ ባሊ ፣ ብረት ምጣድና መጥለቂያ ጣሳ ከሞራ ሳሙና ጋር ይዞ ወደመታጠቢያዋ ክፍል ፤ የራሷ መተዳደሪያ ደንብና ሉአላዊነት አላት። የብዜን ፍርጎ ከአድካሚ ስራ በኋላ ሁለት ሁለት እየተቀላለዱ መታጠብ ...

ታለ እንደሚለው እህቶቹ ሲያድጉ በቤተሰቦቻቸው ቤት የነበርቸው የአኗኗር ስርአት ገላቸውን ሲታጠቡ ሳይቀር የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች በሙሉ አሁን ከሚኖሩት ህይወት እንደሚለያይ ነው::

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳባዊ የስነ ጽሁፍ እሳቤ በተመረጡ የአለማየሁ ገላጋይ ረጅም ልቦለዶች እንዴት እንደተንጸባረቀ ለማሳዬት የተደረገ ነው፡፡ይህን ዓለማ ለማሳካትም ሶስት የአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ተመርጠዋል፡፡ *እነዚህም አጥቢያ(*1999)፣ *በፍቅር ስም(*2009) እና ታለ *በእውነት ስም(*2011)ናቸው፡፡ይህን ሂሳዊ ትንተና ለማካሄድ የማርክሲስት አቀንቃኞች የሚያነሷቸውን ርዕዮተ ዓለም ፣ ቁስ አካላዊነት ፣ ርእዮተ ዓለም እና መደብ የሚሉትን ጭብጦች ከልቦለዶቹ ውስጥ ነቅሶ በማውጣት በታሪኩ ውስጥ በገጸ-ባህሪያት የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ በምን መልኩ ግልጋሎት ላይ እንደዋሉ ተንትኖ ማሳየት ተችሏል፡፡

በጥናቱ ሂደት በልቦለዶቹ ውስጥ ሃይማኖትን ፣ ስርአተ ጾታን እና ኢኮኖሚያዊ መደብን መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የክፍፍልና የብዝበዛ ስርአት ምን እንደሚመስል ማየት ተችሏል፡፡ በዚህም ሃይማኖትን እንደመጠቀሚያ/ሽፋን በማድረግ ስራ መስራት የማይፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ሰረተኛውን የህብረተሰብ ክፍል ብዝበዛ ሲያካሂዱበት ይስተዋላሉ፡፡

በመደብ ውስጥም እንዲሁ ሃብታምና ደሃ ወይም ያላቸውና የሌላቸው ተብለው ተመድበው ያላቸው የተባሉት የተመቻቸ ኑሮ ሲኖሩ ደሆች ደግሞ የተጎሳቆለ ኑሮ ሲኖሩ ተስተውለዋል፡፡ እነዚህ ሃብታም ተብለው የሚጠሩት ሃብትን በውርስ ምክንያት ያከማቹ እንደሆኑም በልቦለዱ ገጸ ባህሪያት ተገልጧል፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ቡርዧ ተብለው የሚጠሩ ናቸው፡፡ እነዚሀ የህብረተሰብ ክፍሎች ምንም እንኳ በቁጥር ከፕሮሌታሪያት የሚያንሱ ቢሆኑም ባላቸው ኢኮኖሚያዊ ኃይል ምክንያት በብዙኃኑ ላይ ብዝበዛ እና ጭቆና እንደሚያደርሱ በልቦለዶቹ ውስጥ ተመላክቷል፡፡

ስርአተ ጾታን ስንመለከት በፌሚኒስት አቀንቃኞች ሴቶች ከወንዶች በተለየ ጭቆና እንደሚደርስባቸው ይናገራሉ፡፡ ከፌሚኒስት ዓይነቶች መካከል አንዱ ማርክሳዊ ፌሚኒስት የሚባለው ነው፡፡ በዚህ ስነ ጽሁፋዊ ሂስ ወቅት ሴቶች በማህበራዊ መደብ ውስጥ ከሚደርስባቸው ጭቆና በተጨማሪ በስርአተ ጾታ ውስጥም ይጨቆናሉ የሚል ነው፡፡ በልቦለዶቹ

ውስጥ ያሉ ሴት ገጸ ባህሪያት ኢኮኖሚያዊ መደቡ ከሚያሳድርባቸው ጫና በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የስርአተ ጾታ ህግ እንድጨቆኑ ሲደርጋቸው መመልከት ተችሏል፡፡

ሌላው በማርክስ ፍልስፍና ውስጥ ተዘውትሮ ስለሚነሳው ቁስ አካላዊነት ከሃሳባዊነት ተለይቶ እንዴት በሰዎች የኑሮ ሂደት ውስት ተግባራዊ እንደሚሆን ታይቷል፡፡ እንደታፈሰ አይነት ያሉ ገጸ ባህሪያት የሰዎች የኑሮ ትስስር በቁሳዊነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ማሳየት ችለዋል፡፡

በአጠቃላይ በ*አጥቢያ* ፣ *በፍቅር ስም* እና *ታለ በእውነት ስም* በተሰኙት የአለማየሁ ገለጋይ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳባዊ የሥነጽሁፍ እሳቤዎች በምን መልኩ እንደቀረቡ የታየባቸው ሥነጽሁፋዊ ስራዎች ናቸው፡፡ በተለይ በአጥቢያ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በዝቅተኛ እና ከፍተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ርዕዮተ ዓለማዊ የመደብ ትግል ሲካሄድ ይታያል፡፡ ይህም ልቦለዶቹ በተጻፉበት ዘመን ያለውን ሃይማኖታዊ ፣ ስርአተ ጾታዊ ፣ መደባዊ እና ቁሳዊ ርዕዮተ አለሞች ምን እንደሚማስሏ ማሳየት ችለዋል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ማርክሲዝም ሊኒኒዝም መዝገበ ቃላት።(1978)።አድስ አበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

ሰብለ ወልደኪዳን።(2010)።*"የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች"* የሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ጽሁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ ።

ቴዎድሮስ ገብሬ።(2001)።"የዘመን መንፈስ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ"። መድብለ ጉባኤ፣ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር።

ትንደድ እድሜ።(2011)።*"ሙስና በያልታበሱ እንባዎች እና በአፈሳማ ልቦለድ ውስጥ"* የሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ጽሁፍ። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ ።

አለማየሁ ገላጋይ።(1999)።*አጥቢያ* ። 3ኛ እትም። አድስ አበባ፣ በ H&F ማተሚያ ቤት ታተመ።

---------------------። (2009) ።*በፍቅር ስም። 5ኛ እትም*።አድስ አበባ፣ በ H&F ማተሚያ ቤት ታተመ።

------------------።(2011)።*ታለ* በእውነት ስም።3ኛ እትም። አድስ አበባ፣በ H&F ማተሚያ ቤት ታተመ።

ዘሪሁን አስፋው።(1992)።*የሥነ ፅሁፍ መሰረታዊያን*።አድስ አበባ ፣ በንግድ ማተሚያድርጅት ታተመ።

የኢትዮጵያ መጽሃፍ ቅዱስ ማህበር።(1980*)።መጽሃፍ ቅዱስ።* አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል።(1993)።*አማርኛ መዝገበ ቃላት*።አዲስአበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ።

Abyie Daniel Ambachew (1986). "*Socialist realism and its implications for the African Writers*": M.A. Thesis, Adiss Abeba University, Unpublished.

Althusser, L.(1971).*Ideology and ideological state Apparatus*: sur la reproduction,London.

Balew Demssie (2009). "*deology and the Representation of Female Characters in Ngugi wa Thiong'o's The River Between and A Grain of Wheat"*. M.A.Thesis. Adiss Abeba University, Unpublished.

Barry, P.(2002).*An introduction to literary and cultural theory*. 2nd edition:

Castle,G.(2007).*The Blackwell Guide to Literary Theory*: Australia,blackwell Publishing Ltd.

Dobie, A. B.(2002).*Theory into Practice an Introduction to Literary Criticism.* 3rd Edition: University of Louisiana at Lafayette.

Eagleton, T. (1996.) *Literary Theory: An Introduction*. 2nd ed. Minneapolis: University of Minnesota Press.

Fisseha Tesfu (2009). "*Ideology in selected east African Anglophone noveles: a Comparative study of post-colonial experience".* P.h.d Thesis, Adiss Abeba University, Unpublished.

Holombers, A. (2005). Doing Gender -A Question of Power. Stockholm: Forum Syds förlag.http://www.ipu.org/press-e/pressrelease201503101.htm

John, T. Ishiyama (Oct 2014). *21st century poletical science: A Reference handbook.* whose work for that encyclopedia formed the basis of his contributions to Britannica. www.britannica.com/topic/social-class

Kiriti, N,(2011). Tabitha W. Institutions and Gender Inequality: A Case Study of the Constituency Development of Fund in Kenya. Addis Ababa: Eclipse Printing Press.

Madsen, D. (2000). *Feminist Theory and Literary Practice*. London: Pluto Press.

Marx, k. and Engels, F. (1848).*The Communist Manifesto*: Moscow, progress Publisher.

Michael Fiquremariam. (2008). "*The study of the influence of Marxism in Bealu Girma's three novels: Haddis, Yekey Kokeb Tiri and Derasiw".* Adiss M.A. Thesis, Abeba University, Unpublished.

Misrak Tatekegn (2002). "*Alienation in three Amharic novels: Fɨkʾɨr ɨskä Mäkʾabɨr, Adäfrɨs and Kadmas Bašagär",* M.A. Thesis, Adiss abeba University, Unpublished.

Muhammed aziz (2017 november 19). Different Types of Social Classes, https://www.yourarticlelibrary.com

Nenola, A.(November 2003). "Folklore and the Genderized World." (1993) In Fekade Azeze. (comp). Readers for EtLi 621: Folklore. Adiss Ababa University,

Olasupo F.A , Victoria Olugbemi Kikelomo & Ajuwon Jumoke Adeniran."Proverbs and Gender Equalities and Equities in African Cultures: Yoruba Culture as A

Case Study." Global Journal of Human Social Science, Arts & Humanities. Global Journals Inc. (USA). Vo. 12.13.10. 2012.

Palmisano, J.M. (ed).(2001) World of Sociology. New York: Farmingto Hills,Vol.1.

Rashmi priya. (2014). Marx's Sociology Theory of Class Struggle. **https://www.yourarticlelibrary.com**

Reeves, H. and Baden, S. (2000) Gender and Development: Concepts and Definitions. Brighton: Institute of Development Studies,

Saylor Foundation.(2013 sebtember 17). Definitions of "marxcism" saylor URL: www.saylor.org/ENGL301 Sub-subunit 2.3.1

Smith, E. (1967). Treasury of name lore; harper and raw. New york.

Tyson, L.(2006). Critical theory today: a user-friendly guide. 2nd ed. USA: Routledg, nework London.

Wellek, R. and Austin. (1995). theory of literature. 3rd ed, San Diego: HBJ books.

www.encyclopedia.com